# አጥቢያ ቤተክርስቲያንህን አጠናክር

## ተጽዕኖ ፈጣሪ ቤተክርስቲያን መሆን

***ለሰርቶ ማሳያው አስተባባሪ የተዘጋጀ መምሪያ***

### ማብራሪያ

አጥቢያ ቤተክርስቲያንህን አጠናክር የተሰኘው ሰርቶ ማሳያ የቤተክርስቲያን መሪዎች ምዕመኑ እግዚአብሔር በጠራው ስፍራ የእግዚአብሔር ወኪል ሆነው የተሰጣቸውን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት ትኩረታቸውን በአንድ አቅጣጫ እንዲያውሉ ለመርዳት ያስችላቸዋል፡፡ ሰርቶ ማሳያው በቃለ እግዚአብሔር መሰረትነት የተዘጋጀ ዓላማ ምንያህል አስፈላጊ አንደሆነ፣ አስሩ የቤተክርስቲያን ጤናማነትን የምንለካባቸውን ባህርያት ለመሪዎች ያስተዋውቃል፣ እንዲሁም መሪዎች ቤተክርስቲያን በማህበረሰቡ ውስጥ ተጨባጭ ተጽዕኖ መፍጠር የምትችል እንደሆነች እንዲገነዘቡ ይጋብዛል፡፡

መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ
ብዙ አጥቢያ ያላት፤ ጠንካራ ቤተክርስቲያን

Revised March 13, 2020

**የአሰልጣኙ መምሪያ**

አጥቢያ ቤተክርስቲያንህን አጠናክር የተሰኘው ሰርቶ ማሳያ የቤተክርስቲያን መሪዎች ምዕመኑ እግዚአብሔር በጠራው ስፍራ የእግዚአብሔር ወኪል ሆነው የተሰጣቸውን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት ትኩረታቸውን በአንድ አቅጣጫ እንዲያውሉ ለመርዳት ያስችላቸዋል፡፡ ሰርቶ ማሳያው በቃለ እግዚአብሔር መሰረትነት የተዘጋጀ ዓላማ ምንያህል አስፈላጊ እንደሆነ፣ አስሩ የቤተክርስቲያን ጤናማነትን የምንለካባቸውን ባህርያት ለመሪዎች ያስተዋውቃል፣ እንዲሁም መሪዎች ቤተክርስቲያን በማህበረሰቡ ውስጥ ተጨባጭ ተጽዕኖ መፍጠር የምትችል እንደሆነች እንዲገነዘቡ ይጋብዛል፡፡

ይህ ማኑዋል በእናት ቤተክርስቲያናቸውም ይሁን በሌሎች ቤተክርስቲያናት ይህን ስልጠና መስጠት ለሚፈልጉ ሰዎች ተጨማሪ ግብአት እና ጥቆማን ይሰጣል፡፡ ይህን ሰርቶ ማሳያ በሚገባ ለመምራት ትፈልግ እንደሆን ባለህበት አገር የሚገኘውን የብዜት መረብ አገልግሎት አስተባባሪ ማግኘት ትችላለህ (ዝርዝራቸውን በመረጃ መረባችን የምታገኝ ይሆናል፡፡) ይህ አገልግሎት ሁለት የስልጠና ኩነቶች ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል እና የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ሪትሪት በሚል ርዕስ ያዘጋጃል ስልጠናም ይሰጣል፡፡ ስለእነዚህ ስልጠናዎችም ቢሆን ከመረጃ መረባችን ወይንም ለዚህ አገልግሎት በአገርህ ተወካይ ሆኖ ከሚገኘው ግለሰብ መረጃ ማግኘት ትችላለህ፡፡

**ለሰርቶ ማሳያው መሪ የተዘጋጁ ግብአቶች፡-**

1. የአሰልጣኙ ማኑዋል

2. የተሳታፊዎች ማኑዋል

3. ተንቀሳቃሽ ጽሑፍ (powere point slides) በመረጃ መረባችን በሲዲ መልክ ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡

4. ስለሁለንተናዊ የቤተክርስቲያን እድገት ስልጠና ከሚሰት ግለሰብ እርዳታ ማግኘት ትችላለህ (በአገርህ ያለው ተወካይን አድራሻ ከመረጃ መረባችን ላይ ማግኘት ትችላለህ)፡

የብዜት መረብ አገልግሎት መጋቢዎችን እና የቤተክርስቲያን መሪዎችን በማሰልጠን የቤተክርስቲያን ተከላን እና እድገትን ይደግፋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመረጃ መረባችን በነጻ ሊወሰዱ እና ሊባዙ የሚችሉ መጽሐፍትን አዘጋጅተናል፤ የመረጃ መረብ አድራሻችንም ይህ ነው www.multiplictionnetwork.org

## ይህን መምሪያ እንዴት ልንጠቀምበት እንችላለን

ይህ መምሪያ ተሳታፊዎችን በዚህ ስርቶ ማሳያ ወቅት ትመራቸው ዘንድ የሚያስችልህን አቅም ይፈጥርልሃል፡፡ እያንዳንዱ ገጽ በተሳታፊዎች ማኑዋል ላይ የሚገኙ መረጃዎችን በዋናው የጽሑፍ ክፍል ሲያሳይ ለመሪው ደግሞ የሚሆን መምሪያ በአነስተኛ መጠን በተጻፉ የጎንዮሽ ማስታወሻዎች በማኑዋሉ ይገኛል፡፡ በተሳታፊዎች ማኑዋል ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች መልሶቻቸውን የሚያገኙት በዚህ ማኑዋል ከስር ተሰምሮባቸው ወይንም (ለምሳሌ፡ <u>እግዚአብሔር</u>) እና ከአንዳንድ ገጾች በታች በአነስተኛ መጠን ባለው ጽሑፍ ተቀምጦ እናገኛለን፡፡

ለእያንዳንዱ ክፍለትምህርት ማኑዋሉ እንደየጊዜ ሁኔታው ተሳታፊዎች በጥንድ (ለሁለት ሆነው) ወይንም አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው ቡድን መስርተው የሚወያዩባቸው እና የሚመልሷቸው ጥያቄዎችን ያቀርባል፡፡ በእርግጥ በእያንዳንዱ ክፍለትምህርት የቀረቡትን ጥያቄዎች በስልጠናው መርሃግብር የሰዓት አጠቃቀም ሁኔታ መወያየት እና መመለስ ስለማይቻል አሰልጣኙ ወሳኝ የሚላቸውን ጥያቄዎች በመምረጥ ተሳታፊዎች በውይይቱ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

እያንዳነዱ አሰልጣኝ የራሱን ልምድ፣ ገላጭ ማሳያ፣ እና ምሳሌዎችን በመጠቀም የስልጠና ማኑዋሉን እንዲያዳብር አበክረን እናሳስባለን፡፡

### የሚመከር የጊዜ ሰንጠረዥ

ለአንድ ቀን ለሚዘጋጅ ስርቶ ማሳያ ሊኖር የሚገባውን የጊዜ መጠን ምን መሆን እንዳለበት ያዘጋጀነው ጥቆማ አለ፡፡ ይሁን እንጂ እናንተ ለሰልጣኞቻችሁ ይሆናል ያላችሁትን የተሻለ የጊዜ አጠቃቀም መወሰን ትችላላችሁ፡፡ ከፈለጋችሁ ደግሞ (አንዱን ክፍለትምህርት በአንድ ሳምንት) በማድረግ ስልጠናውን ከአራት ሳምንታት በበለጠ ጊዜ ውስጥ ማካሄድ ትችላላችሁ፤ የስልጠና ወጪ እንዲቀንስላችሁ ከፈለጋችሁ አርብ ማታ እና ቅዳሜ ጠዋት ስልጠናውን ማድረግ ጥሩ መፍትሄ ይሆናል፡፡

እያንዳንዱ ክፍለትምህርት በአንድ ወይንም በአንድ ተኩል ሰዓት ውስጥ እንዲያልቅ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ስልጠና ማብቂያ ላይ ተሳታፊዎች የምዘና ቅጹን የሚሞሉበትን በቂ ጊዜ አሰልጣኙ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡

የሚቻል ከሆነ በዲጂታል ካሜራ ወይንም ጥርት ያለ ምስል ሊሰጥ በሚችል ሞባይል የሰርቶ ማሳያ ሂደታችሁን በምስል በማስቀረት ለብዜት መረብ አገልግሎት ከመርሃግብሩ ውጤት ሪፖርት ጋር ኢሜይል ማድረግ ትችላላችሁ (እንዴት ሪፖርት እንደሚደረግ እና ለእኛ የምትልኩበትን መንገድ ማወቅ ከፈለጋችሁ በመረጃ መረባችን ወይንም በዚህ ሞጁል ገጽ 31 ላይ ያለውን ቅጽ መመልከት ትችላላችሁ፡፡)

### የሰርቶ ማሳያው ግብአቶች

ዓላማችን ይህ ስርቶ ማሳያ በተቻለ መጠን እጅግ ብዙ ለሆኑ መሪዎች በአነስተኛ ወይንም ምንም ወጪ በሌለው ሁኔታ እንዲዳረስ ነው፡፡ እነዚህን ማኑዋሎች በራሳችሁ ወጪ በማባዛት አሊያም ተባዝቶ የተዘጋጀውን በማባዣ ዋጋ ከብዜት መረብ አገልግሎት በመግዛት፤ ስልጠናው የሚደረግበት ቤተክርስቲያን ደግሞ የሻይ ጊዜ ወጪን በመሸፈን እንድትሳተፍ በማድረግ በቀላሉ ማሰልጠን ይቻላል፡፡

ይህን ግብአት እናንተ ለምታገለግሉት ማህበረሰብ ይሆናል የምትሉትን የሽፋን ስዕል እና ይዘት በማዘጋጀት ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡

## የብዜት መረብ አገልግሎት

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎች የተወሰዱት ከ1954ቱ ትርጉም ሲሆን እንደየ አስፈላጊነቱ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

**ማውጫ**


**ክፍለትምህርት 1** መነሳሳት፣ ራዕይ ተልዕኮ ........ 5

**ክፍለትምህርት 2** የጤናማ ቤተክርስቲያን አምስቱ ግዳጆች ........ 10

**ክፍለትምህርት 3** የጤናማ ቤተክርስቲያን አምስቱ ተግባራት ........ 20

**ክፍለትምህርት 4** ለዋጩ ስርአት ........ 28

መገምገሚያ ቅጽ ........ 41

የምስክር ወረቀት ........ 43


| **ስልጠናውን ለመስጠት የሚመከር የጊዜ ሰንጠረዥ** | |
|---|---|
| ምዝገባ እና እንኳን ደህና መጣችሁ | |
| የአምልኮ እና ጸሎት ጊዜ | 30 ደቂቃ |
| ክፍል 1 | 90 ደቂቃ |
| ክፍል 2 | 90 ደቂቃ |
| **ረፍት** | |
| ክፍል 3 | 90 ደቂቃ |
| ክፍል 4 | 90 ደቂቃ |
| የጥያቄና መልስ፣ ግምገማ እና መዝጊያ ክፍለጊዜ | |

# ክፍለትምህርት 1

# መነሳሳት፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ




### "ሁለንተናዊ የቤተክርስቲያን ዕድገት" ምንድን ነው?

የቤተክርስቲያን እድገት ጤናማ ነው የሚባለው የቤተክርስቲያኒቱ ሕይወት እድገት በሁሉም አቅጣጫ እንዲሆን ማድረግ ሲቻል እንጂ፤ የአባላት ብዛት ወይንም የቤተክርስቲያኒቱን ፕሮግራሞች በሚካፈሉ ሰዎች ብዛት ብቻ የሚለካ አይደለም፡፡ ጤናማ ቤተክርስቲያን ራሱን የሚመለከተው እግዚአብሔር ለዓለም፣ ለሰው ዘር እና ለመላው አጽናፈ ዓለም በሁሉም አቅጣጫ እንዲቀየር በሚያስበው ሰፊ ዓላማ መዳረሻ ልክ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ልዕልና እንደመነሻ አድርጋ፤ በሁሉም የሕይወት አቅጣጫዎች (በቤት፣ በማህበረሰብ፣ በስራ እና በመሳሰሉት) ውስጥ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ የምስራች ቃል ተጽዕኖ በመፍጠር የክርስቶስ አካል ለመሆን የምትሻ ናት፡፡

### የሁለንተናዊ ቤተክርስቲያን እድገት መዳረሻ

ይህ ክፍለትምህርት እግዚአብሔር እንድናከናውነው የጠራንን ስራ ለመፈፀም ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ህብረት እንደሚያስፈልግ ለማስታወስ ይረዳናል፡፡ ለእግዚአብሔር ስራ መነሳሳት በውስጣችን ሲኖር፤ እግዚአብሔር በእኛ ሊሰራ ስለሚፈልገው ወይንም ሊሰራ ለሚችለው ጉዳይ ራዕይ ማዘጋጀት እንችላለን፡፡ ለእግዚአብሔር ጥሪ ታዛዦች ስንሆን፤ ለዓለም ሁሉ የሚሆን ተልዕኮ ይዘን መንቀሳቀስ እንጀምራለን፡፡ ይህ ግን ሊሆን የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር፣ በእኛ እና በማህበረሰባችን መካከል ስላለው ህብረት የሚያስተምረንን በትክክል ስንረዳ ነው፡፡

ይህ ክፍለትምህርት የጤናማ ቤተክርስቲያንን እድገት በማብራራት ነው የተጀመረው፡፡

#### በአንድ ጥግ ዳቦ በሌላ ጥግ ወተት


ሌላው፤ የቤተክርስቲያን እድገት ስልትን እና አውድን ለመጠበቅ የሚቀመርን ስልት ሐሳብን የራስ አድርጎ መውሰደ አስፈላጊነትን አብራራ፡፡

ከአመታ በፊት በአሜሪካ የሚገኙ መደብሮች ሰዎች ብዙ እዲገዟቸው ማድረግ የሚችሉበትን ስልት አገኙ፡፡ ሰዎች ብዙ ጊዜ ለዕለት ተዕለት ፍጆታ የሚጠቀሙበትን እንደ ዳቦ እና ወተት ያሉ ምግቦችን ለመግዛት ሲመጣ፤ እነዚህን የሚያገኙበት ስፍራ እስኪደርስ ድረስ ብዙ ሌሎች የሚሸጡ ቁስ ወይንም ምግቦችን አልፎ የሚሄድ ከሆነ እና ልዩ ቅናሽ ያላቸው ዕቃዎችንም ካገኘ የመግዛት ፍላጎቱ ይጨምራ፡፡ በዚህ ጊዜ እነዚህ ነጋዴዎች የሰዉን የመግዛት ፍላጎት ለመጨመር የተለያዩ ጥናቶችን ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ በንግድ ቦታቸው የሚከፈተው ሙዚቃ (ለስለስ ያለ እና ዝግ ያለ ሙዚቃ ሰዎች ቀስ እያሉ እዲጓዙ ያደርጋል)፣ እቃዎቻቸውን የሚደረድሩበት መንገድ (እንዲሸጥላቸው የሚፈልጉትን እቃ ለደንበኞቻቸው እይታ አመቺ የሆነ ስፍራ ላይ ያስቀምጡታል፡፡)

እንግዲህ ለሰዎች ቁሳቁስ ለመሸጥ ነጋዴዎች ይህን ያህል ተጨንቀው ካጠኑ፤ እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ ሰዎች ክርስቶስን በማወቅ የእርሱ ሕዝቦች ይሆኑ ዘንድ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጥራት የምችለውን ያህል ስለባህርያቸው ማጥናት ምን ያህል ያስፈልገን ይሆን? ምንም እንኳን በክርስቶስ የሚገኝ የሕይወት መልዕክት ባይቀየር እንኳን ባህል እና ሰዎች ነገሮችን የሚከውኑበት መንገድ ይቀየራል፡፡ ስለሆነም ወንጌልን የምንናገርበት፤ የምንደርሳቸውን ሰዎችን አውድ ያማከለ እንዲሆን መቀየር ይኖርበታል፡፡

**ልምምድ፤ ነጥቦቹን አገናኙ**

እነዚህን ነጥቦች እጃችሁን ሳታሳርፉ በአንድ ጊዜ እርሳሳችሁን ከወረቀቱ ሳታነሱ በአራት መስመሮች ብቻ ለማገናኘት ሞክሩ፡፡



**ነጥቦቹን አገናኙ**

ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚገርማቸው እነዚህን ነጥቦች ለመግጠም የግድ ከተከለለው ክልል መውጣት ግድ በመሆኑ ነው፡፡ አንዳንድ ጉዳዮች ከምናስበው የሐሳብ አድማስ ሰፋ አድርገን እንድንመለከት ያስገድደናል- ለእግዚአብሔር ታማኞች እንዲሆን ዘንድ - "ከሳጥን ውጪ ማሰብ" የሚሉት አይነት፤ እያንዳንዳችን ለተልዕኮአችን ታማኝ እንድንሆን እና በአገልግሎታችንም የተሻለ ውጤት እንዳናገኝ እንቅፋ የሚሆንብን በአእምሮአችን ውስጥ ያለ እና የምንገጣጥማቸው ነጥቦች እና የአገልግሎት ፍልስፍናዎች አሉን፡፡

***ራዕይ***

ራዕይ ማለት እግዚአብሔር የእርሱን የመዋጀት አላማ በእናንተ እንዴት እንደሚፈጽም ሊመጣ ያለውን <u>የወደፊቱን</u> መመልከት ነው፡፡

- የመነጽር ሚና
- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በእነርሱ ሊሰራ ስላለው ስራ ራዕይ ያላቸውና ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ ሰዎችን ታሪክ ይዟል፡፡

1. አብርሃም እጅግ ብዙ ትውልድ ሊኖረው፣ ለእነርሱም የሚሆን መሬት እና ለዓለም በረከት መሆን፤ ዘፍ12፡1-3

*ራዕይ የራዕይ ዋናው ዓላማ መሪዎች መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት ያደረገ፣ ግልጽ እና አነቃቂ ራዕይ ሲኖራቸው፤ እግዚአብሔር በአካባቢያቸው እየሰራው ላለው የማዳን ስራ አብሮ ሰራተኛ ይሆኑ ዘንድ ሰዎችን ማንቀሳቀስ እንደሚያስችል እንዲረዱ እድል መስጠት ነው፡፡*

*የመነጽር ሚና፤ አንድ እይታው በመነጽር መደገፍ የሚያስፈልገው ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ መነጽር ሲያደርግ፤ የተሻለ ማየት እንደሚችል ስለሚገነዘብ ከፍተኛ የሆነ መደነቅ ይፈጥርበታል!*

*መጽሐፍ ቅዱስም እንደ መነጽሩ አይነት ተግባር ያለው ይመስላል፡፡*

2. ኖኅ ቤተሰቡን እና እንስሳትን ከጥፋት ውሃ መታደግ፤ ዘፍ 6፡ 13-14፣ 17-20
3. ኢያሱ እና ካሌብ እስራኤል እግዚአብሔር የሰጣቸውን የተስፋውን ምድር ማውረስ፤ ዘኍ 14፡6-9
4. ጳውሎስ በሮም ግዛት ላሉ አህዛብ ሁሉ የምስራቹን ወንጌል ማሰማት፤ ሐዋ 26፡13-18፡፡
5. ኢየሱስ ፈውስን፣ ተስፋን እና አርነትን ለሰው ዘር ሁሉ ማምጣት፤ ሉቃ 4፡18-19፡፡

- ጤናማ ቤተክርስቲያን የሚጀመረው ግልጽና አነቃቂ በሆነ ራዕይ ነው፡፡
- የአናጺው ምሳሌ


*የእግዚአብሔርን መንግስት በመገንባት ሂደት ውስጥ የስራው አካል መሆን ትፈልጋህ?*

*መቼ ነው የመጀመሪያውን ድንጋይ የምታስቀምጠው?*

| |
|---|
| *"ያለእምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና፡፡" ዕብ 11፡6*<br>*"በሰው ልብ ብዙ አለ፤ የእግዚአብሔር ምክር ግን እርሱ ይጸናል፡፡" ምሳ 19፡21* |

**ስዕላዊ መግለጫ፡-** በእግዚአብሔር - ቤተክርስቲያን - ማህበረሰብ መካከል ያለ ግንኙነት

<u>እግዚአብሔር</u>



<u>እኔ/ቤተክርስቲያን</u> <u>ማህበረሰብ</u>

ነገሮችን በቃለእግዚአብሔር መነጽር ስንመለከት (ራሳችንን፣ ሕይወታችንን ገጠመኝ፣ ጎረቤቶቻችንን) በከፍተኛ ሁኔታ የጠራ የማየት አቅም ይኖረናል፡፡ እንዲህ ከሆነ የግል ሕይወታችንም ይሁን ማህበረሰባችንን የምመለከተው እግዚአብሔር እንደሚመለከት ይሆናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት የሌለው ራዕይ የያዘ ቤተክርስቲያን በፍጥነት ወደ የማህበረሰብ ስብስብ (ዕድር ወይም ዕቁብ) መሰል ስብስብ ወይንም የማህበረሰብ ግልጋሎት ወኪል ወይንም መንፈሳዊ "ፈጣን ምግብ" ማግኛ ይሆንና ሰዎች በፈለጉት ጊዜ እየመጡ የፈለጉትን ነገር በፈለጉ ጊዜ እያገኙ የሚሄዱበት ስብስብ ይሆናል፡፡ ከዚህ ይልቅ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን እንፈልግ እንደሆን እግዚአብሔር ናችሁ ባለን ላይ ሕይወታችንንም ይሁን የምዕመኑን ሕይወት ማስተሳሰር ያለብን፡፡ ማህበረ ምዕመናችንም ይሁን ማህበረሰባችንን በእግዚአብሔር አይን ነው ማየት ያለብን፡፡ እግዚአብሔርም እንድንሆን እና እንድንሰራ ነው የጠራን?

የአናጺዎቹ ምሳሌ፤ አንድ ሰው ድንገት ሶስት ድንጋይ እየጠረቡ ያሉ ሰዎች ጋር ጠጋ አለና ምን እየሰሩ እደሆነ ጠየቃቸው፡፡ የመጀመሪያው "ለመኖርና ገንዘብ ለማግኘት ነው የምሰራው" አለው፤ ሁለተኛው ደግሞ "ስራዬ ድንጋይ ጠራቢ ነው፤ ድንጋይ እየጠረብኩ ነው" ብሎ መለሰ፤ ሶስተኛው ሰው ግን እዲህ አለ "ይህች ከተማ በታሪኳ አይታ የማታውቀው ቤተመንግስት እገነባለሁ፡፡" ልክ እዲሁ ብዙዎቻችን ወደቤተክርስቲያን የምንሄደው እግዚአብሔር ለእኛ ተግባር፤ ማለትም ለኑሯችን፣ ቤተሰቦቻችን እና ማህበረሰባችን በኢየሱስ ክርስቶስ የምስራች ወንጌል ይለወጡ ዘንድ በልቡ ያለውን ትልቅ ራዕይ ከግምት ውስጥ ሳናስገባ፤ በጊዜው ልናበረክተው ያሰብነውን ተግባር ብቻ ነው፤ የሰንበት ትምህርት ለማዘጋጀት፣ ለተቸገሩ ሰዎች ምግብ ለማድረስ፣ ገንዘባችንን በአስራትም ይሁን በመባ መልክ ለመስጠት ብለን የአንድ ጊዜ ተግባርን አስበን እንሄዳለን፡፡

በእግዚአብሔር፣ በቤተክርስቲያን እና በማህበረሰብ መካከል ያለ ግንኙነት፤ ይህ ክፍለትምህርት በእግዚአብሔር፣ በቤተክርስቲያን እና በማህበረሰብ መካከል ያለን ግንኙነት ቁልፍ በሆነ ቅደም ተከተል በማስቀመጥ ያብራራል፡፡ ተሳታፊዎችን በዚህ ስልጠና በምትመራበት ወቅት የራስህን ቤተክርስቲያን ልምድ አንደ ምሳሌና ገላጭ አሳብ በመጠቀም ነጥቦቹን በሚገባ ለማስረዳት ተጠቀምባቸው፡፡

ይህ ስዕላዊ መግለጫ በአንድ ምስል ውስጥ ሶስት ግንኙነቶችን የሚያሳይ ነው፡-

1. በቤተክርስቲያን እና በእግዚአብሔር መካከል ያለን ግንኙነት
   መርህ፤ አንድ ማህበረምዕመን በማህበረሰቡ ላይ በጎ ተጽዕኖ ማሳደር ይፈልግ እንደሆን፤ ከእግዚአብሔር ጋር የጠለቀ ግንኙነት ከመፍጠር በላይ ምንም አይነት አስፈላጊ ነገር አይገኝም፡፡

> “እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡፡ ያለእኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና” ዮሐ 15፡5
> “እግዚአብሔር ቤትን ካልሰራ ሰራተኞች በከንቱ ይደከማሉ፡፡” መዝ 127፡1

በቤተክርስቲያን እና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ግንኙነት፤ ተሳታፊዎች የቤተክርስቲያንን እና የእግዚአብሔርን ግንኙነት የሚያወሱ ቁልፍ ጥቅሶችን እንዲያነብቡ አድርግ፡፡ ይህ ግንኙነት ቤተክርስቲያን ማንነቷን፣ ራዕይና መነሳሳቷን ጠብቃ እንድትኖር የሚያደርጋት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ በእርሱ ላይ ከተደገፍን በፍጹም ተልዕኮአችንን መፈጸም አንችልም፡፡ ታላላቅ ወንጌላውያን፣ መጋቢያን እና የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ታላቅ የሆኑበት ሚስጥር፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ተንከባክበው ማሳደግ መቻላቸው ነው፡፡ በጸሎት እና ቃለእግዚአብሔርን በማጥናት ከእግዚአብሔር ጋር ለማውራት ጊዜ መውሰድ እርሱን ለማወቅ፣ ፈቃዱን ለማወቅና እርሱን የምናገለግልበት ኃይል ለማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡

2. በእግዚአብሔር እና በማህበረሰብ መካከል ያለ ግንኙነት
   መርህ፤ እግዚአብሔር ሁሌም በዙሪያችን እየሰራ ይገኛል፡፡ አንድ ወንጌላዊ ወይንም የተልዕኮ አገልጋይ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚሄድበት ስፍራ ከመድረሱ በፊት እግዚአብሔር ከብዙ ዘመን በፊት እዚያ በስራ ላይ ነበር፤ አሁንም ይሰራል፡፡
   የኢየሱስ በስጋ የመገለጥ ምሳሌአዊነት - ፊሊ 2፡5-8

> “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፡፡” ዮሐ 3፡16
> “ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግስትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር፡፡” ማቴ 9፡35
> “ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው፡፡” ማቴ 9፡36

በእግዚአብሔር እና በማህበረሰብ መካከል ስላለ ግንኙነት የሚያወሳ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቡ፡፡ እግዚአብሔር ለጠፉት የሚያዝን ልብ አለው፡፡ በኢየሱስ አገልግሎት አማካይነት ወደ ጠፉት፣ ወደታመሙት እና በሰዎች ወደተናቁት፤ ይፈውሳቸው እና እንደገና ያቆማቸው ዘንድ እነርሱን ይፈልግ ነበር፡፡ እኛ ማህበረሰባችን ጋር ከመድረሳችን በፊት እግዚአብሔር በልባቸው መስራት የሚገባውን ይሰራል፡፡ እርሱ የጠራን እርሱ በሚሰራው ስራ ውስጥ አብሮ ሰራተኛ እንድንሆን ነው፤ በዚህም በእኛ ሌሎችን በወንጌል ለመድረስ በምናደርገው ጥረት በእኛ ውስጥ መስራቱን ይቀጥላል፡፡

3. በቤተክርስቲያን እና በማህበረሰብ መካከል ያለ ግንኙነት
   መርህ፤ እግዚአብሔር በእኛ ሆኖ በምድር መመላለስ ይፈልጋል፡፡ እኛ በዚህ ምድር የእርሱ እጅ፣ እግር እና ድምጽ ነን፡፡ አንድ ትልቅ ነገር ከመፈጸማችን በፊት በጥቂት ነገሮች የታመንን መሆን አለብን፡፡


በቤተክርስቲያን እና በማህበረሰብ መካከል ያለ ግንኙነት፤ በመጨረሻም ቤተክርስቲያን ከማህበረሰብ ጋር ያላትን ግንኙነት የሚያወሱ የመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅሶችን አንብቡ፡፡ እግዚአብሔር ባስቀመጠን ማህበረሰብ ውስጥ የእርሱ እጅ፣ እግር እና ድምጽ እንድንሆን ነው የጠራን፡፡ ከተሳታፊዎች መካከል አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነቷን ተንከባክባ የምታሳድግ ቤተክርስቲያን የሚያውቀውን እንደምሳሌ እንዲያነሳ ጠይቅ፤ እንዲሁም በዚህ ህብረታቸው ለማህረሰባቸው የእግዚአብሔር እጅ እና እግር ሆነው እንደሆን እንዲነጋገሩ እድል ስጥ፡፡

ኢየሱስ ለሰማያዊ አባቱ እዲህ አለ “ወደ ዓለም እንደላክኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው” ዮሐ 17፡8

"የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል፡፡"

"ጌታውም መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው፡፡"

ገላጭ ስዕል፤ መነሳሳት፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ




መነሳሳት፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ፤ ይህ ክፍለትምህርት የቤተክርስቲያንን ተልዕኮ ጠቅለል አድርጎ በሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫን ያብራራል፡፡ ስዕላዊው መግለጫ በሚከተለው መንገድ ተብራርቷል፡፡

1. ከእግዚአብሔር ጋር ካላት ህብረት የተነሳ ቤተክርስቲያን እርሱን ለማገልገል ከፍተኛ **መነሳሳት** አላት፡፡ ማህበረሰቡ ደግሞ ይህን መነሳሳቷን በተግባር ይመለከታል፤ ይህ ተግባሯደግሞእንደ **ምስክርነት** ያገለግላል፡፡
2. እግዚአብሔር በማህበረሰብ ውስጥ እየሰራ ይገኛል፤ ቤተክርስቲያን ደግሞ እግዚአብሔር በምድር ላይ እየሰራ ያለውን በመገንዘብ፤ ከዚህ ግንዛቤዋ ውስጥ ***ራዕይን*** ታገኛለች፡፡ ይህ ደግሞ ለቤተክርስቲያን የመኖርን **ዓላማ** ይሰጣታል፡፡
3. እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የእርሱን ተልዕኮ ይዛ በማህበረሰብ ውስጥ እንድትንቀሳቀስ ሲያደርግ፤ ቤተክርስቲያን ደግሞ ይህን **ተልዕኮ** ይዛ ለመንቀሳቀስ ስትፈቅድ የዚያን ጊዜ እግዚአብሔር **በረከቱን** በቤተክርስቲያን ላይ ያፈሳል፡፡
4. ሁሉም ነገር በመስቀሉ እና በኢየሱስ ክርስቶስ መልዕክት ዙሪያ ያጠነጥናል

የፍሎረንስ ቻድዊክ ታሪክ፤ በወርሃ ሰኔ 1952 እ.ኤ.አ ፍሎረንስ ቻድዊክ ካሊፎርኒያ የተሰኘችን የአሜሪካ ግዛት አካል የሆነውን እና 22 ማይል የሚረዝመውን የባህር ዳርቻን በዋና የማቋረጥ ህልም ይዛ ወደ ውሃው ተወርውራ ገባች፡፡ እርሷዋናውን ከጀመረችበት ሰአት አንስቶ የተለያዩ የውሃ ማለፊያ ዋሻዎችን፣ ወንዞችን እና ሐይቆችን አቋርጣለች፤ ይሁን እንጂ ይህ ቀን የተለየ ነበር፡፡

እንዲህ የሚመስል ገጠመኝ በቤተክርስቲያንም ሊገጥም ይችላል፤ ስለሆነም በማህበረ ምዕመኑ የቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሚፈጠረውን ምልክት አንዱን ወይንም ሁለቱን ሳይሆን ሁሉንም ማጤን ተገቢ ነው፡፡

ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ህብረት ሲኖራት፤ እግዚአብሔር ላስቀመጠው ተልዕኮ የተነሳሳች ትሆናለች፡፡ እግዚአብሔር ለማህበረሰቡ ያለውን ዓላማ ቤተክርስቲያን ስትረዳ ራዕይ አላት ማለት እንችላለን፡፡ ከዚያም ማህበረምዕመኑ ይህን ተልዕኮ ለማህበረሰቡ ለማድረስ ዝግጁ ይሆናል፡፡ ቤተክርስቲያን ላለችበት ማህበረሰብ እና ለዓለም ምስክር ስትሆን የእግዚአብሔር በረከት ቤተክርስቲያኒቱ ትሰፋ ዘንድ ይትረፈረፋል፡፡

ማጠቃለያ፡-

የፍሎረንስ ቻድዊክ ታሪክ፤ 1960 ዓ.ም 1952 እ.ኤ.አ፣ ካታሊና ደሴት

***ተግዳሮት፡-***

ዛሬ ካልሆነ፤ መቼ? እኔ ካልሆንኩ ማን?

# ክፍለትምህርት 2

# አምስቱ የጤናማ ቤተክርስቲያን ግዴታዎች

*መግቢያ*

ይህ ክፍለትምህርት አንድ ጤናማ ቤተክርስቲያን ስለሚኖራት አምስት ግዴታዎች ዝርዝር ያስቀምጥልናል፡-

1. ግልጽ እና አነቃቂ ራዕይ
2. መሪዎችን ማንቀሳቀስ
3. የአገልግሎት አካላትን ማንቀሳቀስ
4. ተገቢ የሆነ የግብአት ባላደራነት
5. በአውድ እና አውዳዊነት መካከል ያለ መዋደድ

እነዚህን ግዴታዎች መረዳት መሪዎች ስልታዊ እቅድ እንዲነድፉ እና አገልግሎታቸውን እንዲመዝኑ ያስችላቸዋል፡፡



ምሳሌ፤ በባቡር ሃዲዱ ላይ ይጓዝ የነበረው ሰው፡፡

ጤናማ እና የሚያድግ ቤተክርስቲያን ይኖረን ዘንድ፤ ስለሁሉም የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ እና አገልግሎት ክፍሎች ትኩረት መስጠት ግድ ይለናል (አምስቱ ግዴታዎች እና አምስቱ ተግባራት)፡፡

በባር ሃዲድ ላይ ይጓዝ የነበረው ግለሰብ


በአንድ ወቅት በባቡር ሃዲድ ላይ የእግር ጉዞ ለማድረግ የመረጠ አንድ ግለሰብ ነበር፡፡ ታዲያ ጉዞውን በማድረግ ላይ ሳለ የባቡር ሃዲዱ በስሱ መንቀጥቀጥ ጀመረ፤ ታዲያ ይህ ሰው ይህን መንቀጥቀጥ አስተውሎ ዞር ዞር ብሎ ቢመለከት ምንም አይነት ባቡር አላየም፡፡ በዚህ ምክንያት ይህን ችላ ብሎ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ ከዚህ የመንቀጥቀጥ ምልክት ቀጥሎ በቅርቡ የሚመስል የባቡር ድምጽ ሰማ ታዲያ ተረጋግቶ ቀና ብሎ ቢመለከት አሁንም ከፊቱ ምንም አይነት ባቡር የለም፤ ሰውዮው ይህንንም ምልክት ችላ ብሎ በባቡር ሃዲዱ ላይ የሚያደርገውን ጉዞ ቀጠለ፡፡ ከዚያ ምን የተፈጠረ ይመስላችኋል መልሱ በባቡር መጨፍለቅ ነዋ፡፡ ሰውዬው ያመነው ከፊቱ የሚያየውን ብቻ ስለነበር ሕይወቱን የሚያሳጣው አደጋ ከኋላው እየመጣ እንደነበር ማስተዋል አልቻለም፡፡ በዙሪያችን የሚያንዣብበውን አደጋ አለማስተዋል ውጤቱ ጥፋት ነው! በተመሳሳይ በቤተክርስቲያናችን ከሚፈጠሩ አንድ ወይንም ሁለት ምልክቶች ይልቅ እያንዳንዱን የአደጋ ምልክት በሚገባ ማስተዋል ወሳኝ ነው፡፡

የክፍለትምህርት 2 እና 3 ዋናው ነጥብ የሚያድግ ቤተክርስቲያን ለመትከል የቤተክርስቲያቱ ሕይወት ዙሪያመለስ በጥንቃቄ መጠበቅ እና መንከባከብ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ ካልሆነ ግን ቤተክርስቲያ መላ አካሏ ታማሚ ይሆናል፡፡

አስሩ የቤተክርስቲያን ጤና ማሳያዎች (5 መስጠት በክፍለትምርት 2 እና 5 ተግባራት በክፍለትምህርት 3) የማህበረምዕመኑ ብስለት ደረጃው ምንም ይሁን፤ ሁሉም የተያያዙ እና ሁሉም ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ ናቸው፡፡

እያንዳንዱን ይዘት እና ተግባራትን ከዘረዘርን በኋላ፤ ተሳታፊዎች የራሳቸውን ቤተክርስቲያን መገምገም የሚያስችላቸው ጥቂት አርፍተነገሮች ይገኛሉ፡፡

ስዕላዊ መግለጫ፤ "የጤናማ ቤተክርስቲያን ወሳኝ ምልክቶች"




1. ግልጽ እና አነቃቂ ራዕይ፤ 1ጴጥ 2፡9፣12

ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር የጠራት ጥሪ ያለምንም ብዥታ ሚታያት እግዚአብሔር ባስቀመጣት ጊዜ እና ቦታ የክርስቶስ አካልነቷን የሚያስመሰክር ተግባር ስትፈጽም ነው፡፡ ይህ ራዕይ ከእግዚአብሔር የመዋጀት ዓላማ ጋር የሚስማማና ቤተክርስቲያን በተልዕኮዋ ላይ እንድታተኩር የሚያደርጋት ነው፡፡ በጤናማ ቤተክርስቲያን ውስጥ ስለአገልግሎት ዘርፎች የሚወሰን ውሳኔ፣ በጀት፣ ስለሕንፃ ወ.ዘ.ተ... የሚተላለፍ ውሳኔ ሁሉ ራዕይን ያገናዘበ ነው፡፡

ግልጽ እና አነቃቂ ራዕይ፤ የራዕይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ስነመለኮታዊ አቅጣጫዎች - እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ምን እንድትሆን እና እንድትሰራ ነው የጠራት የሚለው በክፍለትምህርት አንድ ቀርቧል፡፡ አሁን ደግሞ ለአንድ ቤተክርስቲያን ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር ያለውን ሚና እንዳስሳለን፡፡ የራዕይ ቁልፍ ይዘቶች እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረን ጋር የሚስማሙ ናቸው፤ ይህም ግልጽ ትርጓሜ ያላቸው፣ ደግሞ ደጋግሞ የተላለፈ እና በማህበረምዕመኑ እና በመሪዎች ተቀባይነት ያገኙ፡፡

ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር ለመተንተን፤ በቀላሉ የቀረበ ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር እንዴት አድርጎ 8 ቁልፍ ጉዳዮችን እደሚተነትን ሊያስረዱ የሚችሉ ሰዎችን ጋብዝ፡፡ ወደፊት ልንደርስበት ያሰብነውን መዳረሻ በአይነ ህሊናችን እንድንመለከት ያስችላል? ሰዎች ነገሮችን እግዚአብሔር እንደሚያይ እንዲያዩ ያስችላል? በእግዚአብሔር የመዋጀት ዓላማን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው? ወ.ዘ.ተ...

ስምንቱ የራዕይ ገላጭ አርፍተነገር ባህርያት

1. ለመድረስ ያሰብነውን የወደፊት መዳረሻ ጥርት ያለ ስዕል ያሳያል፡፡

2. እግዚአብሔር በሚመለከትበት "መነጽር" አጋጣሚዎቻችንን ማሰብ ያስችለናል፡፡

3. መሰረቱን የሚያደርገው በእግዚአብሔር የመዋጀት ዓላማ ላይ ነው፡፡

4. ነገሮች አሁን ባሉበት የእድገት ሁኔታ (ነገሮች አሁን ባሉበት ሁኔታ) የሚረካ አይደለም፡፡

5. እምነትን ይጠይቃል፡፡

6. ቀለል ባለ መልክ ለሌሎች የሚቀርብ ነው፡፡

7. ሰዎችን ወደ ጸሎት እና ተግባር ያንቀሳቅሳል/ የጊዜን ማለቅ የሚጠቁምና የሚያነሳሳ ነው፡፡

8. በመሪዎች እና አባላት የሚጋሩት ነው፡፡

***ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር ለትንተና፡-***

*"ራዕያችን በከተማችን ያሉ ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ክርስቶስ ኢየሱስን አንደ አዳኝ እና ጌታ እንዲቀበሉ፣ በእርሱ ዕውቀት እንዲያውቁ እና ችሎታቸውንና ያላቸውን ግብአት ለእርሱ ክብር የሚያውሉበት እድል እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡"*

ልምምድ፤ የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት ከግምት አስገባ

እያንዳንዱን አርፍተነገር በማንበብ ሐሳብህን አመላክት ("1" ከአርፍተነገሩ ጋር ሙሉ ለሙሉ እንደማትስማማ ያሳያል፤ "10" መሉለሙሉ እንደምትስማሙ ያመላክታል፡፡)

- ቤተክርስቲያናችን ስለወደፊት እድገቷ ግልጽ እና ተጨባጭ የሆነ ራዕይ አላት

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

- የቤተክርስቲያቱን የወደፊት እድገት ሳስብ በጣም እበረታታለሁ

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

መሪነትን ማንቀሳቀስ፤ ኤፌ 4፡11012

ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር በተጠሩ፣ ራዕዩን በተረዱ፣ የተረዱትን ራዕይ ለምዕመኑ ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያስተላልፉ እና የሚመሩትን ህዝብ በማስተባበር ይህን ራዕይ እውን ለማድረግ በሚሰሩ መሪዎች ግልጋሎት ታገኛለች፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው መሪዎች ባህርያት፡-

1. መሪ ከእግዚአብሔር የተላከ ነው (ዮሐ 17፡18)

2. መሪ አገልጋይ ነው (ፊል 2፡5-8፤ ማር 10፡42-45፤ ዮሐ 13፡14-15)

3. መሪ የእግዚአብሔርን ምሪት ይሻል (መዝ 25፡4-5)

4. መሪ የእግዚአብሔርን ህዝብ የሚያነሳሳ እና የሚያስታጥቅ ነው (ኤፌ 4፡11-12፤ 2ጢሞ 2፡2)

የመሪነት ጥሪን እንደሚገባ ማንቀሳቀስ፤ ኤፌ 4፡ 11-12 ያለው ክፍል የመሪነት ሚና መዕመናንን ማሰልጠን እና ለአገለግሎት ማስማራት ለማስተማር የተጻፈ እደሆነ ትኩረት ሰጥተህ አስረዳ፡፡ የመሪዎች ስራ የቤተክርስቲያኒቱን ራዕይ ምን እንደሆነ ማወቅ፣ ለማህበረ ምዕመኑ ግልጥ በሆነ መንገድ ማስረዳት እና አባላት ራዕይውን ዕውን ለማድረግ ያላቸውን ስጦታ (ተሰጥኦ) እና የግብአት አቅም እንዲጠቀሙ ማደራጀት ነው፡፡ “ሁሉንም ራስህ ስራው” የተሰኙ መጋበ¡ያን ዘመን አብቅቶ የመንገድ ጠራጊዎች ዘመን እነሆ መጣ፡፡ መጋቢው ሁሉን ነገር በራሱ ለመስራት ከእንግዲህ አያስፈልገውም፤ ይልቁን ሌሎች ያላቸውን ችሎታ እና ስጦታ በመጠቀም እዲያገለግሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡ እያንዳንዱ ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥም ይሁን ከቤተክርስቲያን ውጪ ለሌላው በረከት መሆን የሚገባው ስጦታ አለው፡፡

**የመሪነት ዘይቤ ልዩነት**

| | |
|---|---|
| ባለስልጣ መሪ | አገልጋይ መሪ |
| "ተከተሉኝ!" ይላል | "ኢየሱስን እንከተል!" ይላል |
| የእርሱ ራዕይ እና ግብ የቤተክርስቲያኒቱ እንዲሆን ይወስናል | እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ያለውን ራዕይ እና ግብ በመንፈስ ለመረዳት ከመሪዎች ጋር አብሮ ይሰራል፡፡ |
| ለሰዎች የተለያየ ኃላፊነት አይሰጥም፤ ሁሉንም ጉዳይ በራሱ ትዕዛዝ ያሰራል | ሌሎችን ያሳትፋል |
| ውሳኔዎችን ሁሉ በራሱ ይወስናል | ሌሎችን በውሳኔ ሰጪነት እንዲሳተፉ ይጋብዛል |
| ማህበረምዕመኑ በሚያገኘው ድካም ላይ ሁልጊዜ ያጉረመርማል | ማህበረምዕመኑ በሚያገኘው ድካም ከመፍረድ ይልቅ ከድካም ለማውጣት ይጥራል |

| | |
|---|---|
| ሁሉንም ነገር በራሱ ይሰራል፡- ይሰብካ፣ ይጎበኛል፣ ይጸልያል፣ ያስተምራል፣ አምልኮ ይመራል ወ.ዘ.ተ.... | ሌሎችን ለአገልግሎት ለማብቃት ያሰለጥናል ዕውቅና ሰጥቶ ያሰማራል፡፡ |
| ሌሎች መሪዎችን እንደ ተወዳዳሪ እና ስጋት ይመለከታል | ሌሎች መሪዎችን እንደ አብሮ ሰራተኛ እና በረከት ይቆጥራቸዋል |

በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ተግባራትን ሁሉ መጋቢዎች/

አገልጋዮች ብቻ ናቸው መስራት የሚችሉት ብሎ ማሰብ ሞኝነት ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት የሌለው ሐሳብ ነው፡፡ ሙሴ በዘጸ 18፡13-27 ህዝቡ የሚፈልገውን ትኩረት እንዲያገኝ እና እርሱም በስራ ብዛት መስራት የማይችልበት የድካም ጥግ እንዳይደርስ ሌሎችን ለኃላፊነት ማብቃት እንዴት እንደሚችል መማር ነበረበት፡፡

ሐሳብህን ግለጽ፤ ሌሎችን ወደ ስራ ታሰማራለህ? በቤተክርስቲያንህ ካሉ ሰዎች እነማንን በተለያየ መንገድ በአገልግሎትህ ልታሳትፍ ትችላለህ?

የተነቃቃ የአገልግሎት አካል፤ የቤተክርቲያኒቱ አባላት የጸጋ ስጦታቸውን በማህበረምዕምናንም ዘንድ ይሁን በማህረሰቡ ውስጥ ባላቸው ግንኙነት በጥንቃቄ ለመጠቀም በጋራ ይሰራሉ፡፡ እንዳንዱ ተሳታፊ የተሰጠው የጸጋ ስጦታ ምን እደሆነ ማወቁ እጅግ አስፈላጊ እደሆነ ትኩረት ሰጥተህ አስተምር፡፡

መልመጃ፤ የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት መዝን

- ለወደፊት መሪ ይሆናሉ ተብለው የሚጠበቁ ሰዎች ተመርጠው እየሰለጠኑ ይገኛሉ

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

- መሪዎች በቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት ውስጥ በንቃት መሳተፍ የሚፈልጉ ሰዎችን ይመራሉ ይረዳሉም

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

3. የአገልግሎት አካላትን ማነቃቃት፤ 1ቆሮ 12:7፤ 1ጴጥ 4:10 -11

የቤተክርስቲያኒቱ አባላት በኅብረት ይሰራሉ፤ የጸጋ ስጦታቸውንም በቤተክርስቲያን እና በማህበረሰቡ ውስጥ ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ይጠቀማሉ፡፡ ውጤት ተኮር የሆነ መጋቢ አባላቱን እንዴት አድርጎ ማነሳሳት እና ለኃላፊነት ማብቃት እንዳለበት ያውቃል፡፡ ውጤት ተኮር አገልጋዮች የጸጋ ስጦታቸውን መጠቀም ይችሉ ዘንድ ሌሎችን ለአገልግሎት ይሾማል፡፡

**በቡድን በመሳተፍ የሚሰራ ውጤታማ ስራ፡-**

1. ግልጽ እና አነቃቂ ራዕይ

2. ውጤት ለማስመዝገብ በተደራጀ ሁኔታ መስራት

3. ብቁ የሆኑ አባላት

4. የሁሉም አባላት መሰጠት

5. አሳታፊ የሆነ ከባቢ

6. የልዕቀት መመዘኛ

7. አገልጋይ መሪነት

*መልመጃ፤ የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት መዝን*

- ቤተክርስቲያን አባላቶች ለአገልግሎት የተጠሩበትን ጸጋ እንዲያውቁ ታግዛለች

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

- ቤተክርስቲያንን እና ማህበረሰቡን ለማገልገል ስልጠና እየሰለጠንኩ ነው

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

*መልመጃ፤ አባላትን ወደ አገልግሎት ማንቀሳቀስ*

*መመሪያዎች፤* አሁን በቤተክርስቲያንህ እየተተገበሩ ስላሉ የአገልግሎት ዘርፎች አስቡና ከታች ካሉት ምድቦች ውስጥ በአንዱ ውስጥ አስፍሩ፡፡

| ሰዎችን መቀበል | ሰዎችን ማብቃት | ሰዎችን ማስታጠቅ | ሰዎችን ማንቀሳቀስ |
|---|---|---|---|
| ሰዎች ካለህበት ማህበረምዕመን ጋር መገናኘት የሚችሉበት መንገድ፣ መምጣታቸው ሁሉ | ሰዎችን ደቀመዝሙር ማድረግ እና በእምነታቸው እንዲጎለብቱ ማገዝ (የመጽሐፍ ቅዱስ | ሰዎችን ለአንድ የተለየ አገልግሎት ማሰልጠን እና ጥሪያቸውን እንዲለዩና እንዲያደረጁ | ሰዎች የጸጋ ስጦታቸውን በቤተክርስቲያን ውስጥ እና ከቤተክርስቲያን ውጪ ሊጠቀሙባቸው |

የሚከተለውን ታሪክ አካፍል፤ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን መሪ ለተሳታፊዎቹ ሁሉ የታሸገ ስጦታ ከሰጣቸው በኋላ እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው “በዚህ ስጦታ ምን ልንሰራበት እንችላን?” እርግጥ ነው ምን እንደሚሰሩበት ለማወቅ እሽጉን መፍታት ይገባቸዋል፡፡ ከዚያም ሁሉም የተሰጣቸውን ስጦታ ማሸጊያ ሲፈቱ ለእያንዳንዳቸው ከተገጣጣሚ የስዕል እንቆቅልሽ (ፐዝል) ውስጥ አንድ ተገጣሚ ነው የደረሳቸው፡፡ የቡድን መሪው የደረሳቸውን ይህን ስጦታ ምን እንደሚያደርጉ ሲጠይቃቸው፤ ሁሉም የደረሳቸውን የስዕል እንቆቅልሽ በአንድነት በማምጣት መገጣጠም ጀመሩ፡፡ ይሁን እንጂ የሚፈለገው መልክ እና መልዕክት አልመጣም ወይን የጎደሉ የእንቆቅልሹ ክፍሎች ነበረ፡፡ በዚህ ጊዜ የቡድን መሪው እንዲህ አለ “እንግዲህ የቤተክርስቲያንም ተልዕኮ ሙሉ ይሆን ዘንድ ብዙዎችን ወደክርስቶስ ማምጣት ግድ ይለናል!”

እንዲህ ብለህ ጠይቅ፤ እያንዳንዱ ክርስቲያን ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ስጦታ አለው፤ የአንተ/አንቺ ስጦታ ምንድን ነው? የእናንተ ቤተክርስቲያን ሰዎች የጸጋ ስጦታቸውን እንዲያውቁ እና እንዲጠቀሙ ታግዛለች?

| | | | |
|---|---|---|---|
| የተደሰተበት እንደሆነ ለማሳየት እና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ህብረት እንዲኖራቸው መጋበዝ (ምሳሌዎች:- ልዩ አምልኮ ሲኖር፣ የመዝሙር ኮንሰርቶች፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶች፣ ካላመኑ ጋር ህብረት ለማድረግ፣ የቤት ለቤት ወንጌል ስርጭት ወ.ዘ.ተ…) | ጥናት ቡድን፣ ሰንበት ትምህርት፣ የጸሎት ጓድ፣ የአዳዲስ አባላት ትምህርት ክፍል፣ የሴቶች አገልግሎት፣ የወንዶች አገልግሎት፣ የአማካሪና ደጋፊ አገልግሎት ወ.ዘ.ተ…) | የሚችሉበት መንገድ (የወንጌል ስርጭት ሰርቶ ማሳያ፣ ስለመንፈሳዊ ስጦታ የተዘጋጀ ትምህርት፣ ለቤተሰብ የሚዘጋጅ የገንዘብ አያያዝ ሴሚናር፣ ሰዎች ሰርቶ ማሳያ ፕሮግራሞችን መስራትን ወይንም አሰባበክን ማሰልጠን፣ አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን አመራርን ማሰልጠን፣ ወ.ዘ.ተ…) | የሚችሉባቸው መንገዶች (ገበታ ማዘጋጀት፣ ቤተሰቦችን መጎብኘት፣ ማስተማር፣ የዝማሬ አምልኮን መምራት፣ ጥሩ አቅም እንዳላቸው ባመኑበት ጉዳይ አንድን ክፍል በዚህ ዙሪያ ተግባራትን ያከናውኑ ዘንድ መርዳት፣ ለልጆች የእግር ኳስ ስልጠና ማዘጋጀት፣ የጽዳት አገልግሎት፣ ወ.ዘ.ተ…)፡፡ ማንኛውም ሰዎች መስራት የሚችሉት ነገር ሁሉ በቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ መካተት ይችላል! |

ከዚህ በመቀጠል ቤተክርስቲያናችሁ በየትኞቹ መስኮች ውጤታማ እንደሆነች እና በየትኞቹ ደግሞ መስተካከል የሚገባቸው እንዳሉ ተመልከቱ፡፡

| ሰዎችን መቀበል | ሰዎችን ማብቃት | ሰዎችን ማስታጠቅ | ሰዎችን ማንቀሳቀስ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

ከቤተክርስቲያናችሁ መሪዎች ጋር በመሆን አባላትን በቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ማንቀሳቀስ የሚለውን መልመጃ ደግማችሁ ስሩት፡-

1. ቤተክርስቲያናችሁ ለእያንዳንዱ አገልግሎት ዘርፍ ያላትን ተግባራ ዝርዝር ጻፉ

2. ከላይ የዘረዘርካቸው እያንዳንዳቸው ተግባራት በየስፍራቸው ውጤታማ መሆን አለመሆናቸውን ጠይቅ፡፡

3. የትኞቹን ተግባራት ውጤታማ ለማድረግ ወስን፤ ምን መደረግ እንዳለበት አመላክት፡፡

4. ተገቢ የሆነ የግብአት ባለአደራ፤ 1ቆሮ 4፡2፤ ምሳሌ 3፡9-10፤ 1ቆሮ 6፡19-20፤ ሐዋ 20፡35

ቤተክርስቲያን ማህበረምዕመኗ ያላትን ንብረት እና የራሳቸውንም ሃብት በመጠበቁ ረገድ መልካም ባለአደራ እንዲሆኑ ትመራለች ትከታተላለች፡፡ ሁሉም ክርስቲያን እኚህን ሃብቶች (ጊዜ፣ ቸሎታ/ተሰጥኦ እና ሃብት) በእግዚአብሔር መንግስት፤ በቤተክርስቲያንም ይሁን በማህበረሰባቸው ውስጥ ያላቸውን ስራ መጠቀም ይችላል፡፡ ቤተክርስቲያን ራሷም ብትሆን ያላትን ሃብት በጥበብ እና በግልጽነት መጠቀም ይጠበቅባታል፡፡

አባላትን ወደ አገልግሎት ማንቀሳቀስ (ቀጣይ ገጽ)፤ ሁሉም የቤተክርስቲያናት አባላት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነትን መንከባከብ እና ማደግ (ደቀመዝሙር መሆን)፣ ለአገልግሎት የሚጠቅማቸውን ስልጠና ማግኘት እና የተሰጠውን የጸጋ ስጦታ የሚያካፍልበት(የሚጠቀምበት) የአገልግሎት ዘርፍ ያገኝ ዘንድ ሊረዳ ይገባዋል፡፡ ተሳታፊዎች አገልግሎቻቸውን ከሚደግፍ አጋር ወይንም ደግሞ ጥንድ ሆነው አሊያ በቡድን ቤተክርስቲያናቸው በምን እንዴት አድርጋ እያንዳንዱን የአገልሎት ክፍል በሙላት እንዲሰራ እደምታደርግ ለማወቅ ጊዜ ይውሰዱ፡፡ ከዚያ የትኞቹ ክፍሎች በቂ እንቅስቃሴ አላቸው የትኞቹስ ብዙ ትኩረት ይሻሉ፡፡

ተቀባይነት ያለው የግብአት ባላደራ፤ ቤተክርስቲያን አባሎቿ ባላቸው ግብአት/ሃብት ማለትም ጊዜ፣ ንብረት፣ ችሎታ እና የእግዚአብሔር መቅደስ (አካላቸውን) ታማኝ ባላደራ ይሆኑ ዘንድ አጥብቃ ማሳሰብ ይገባታል፤

አራቱ የባለአደራነት መለኪያዎች:-

1. ጊዜ

2. ችሎታ/ተሰጥኦ

3. ግብአት/ሃብት

4. የእግዚአብሔር መቅደስ (ሰውነታችን/አካላችን)

መልመጃ፤ የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት መዝን

- ቤተክርስቲያናችን ገንዘብን በማስተዳደሩ ረገድ የመልካም ባለአደራነት ተግባሯን በሚገባ እየተወጣች ነው

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

- ቤተክርስቲያናችን ስለባለአደራነት እና አስራት በቋሚነት ታስተምራለች

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

5. አውድን እና አውዳዊነትን ማስተሳሰር፤ 2ጢሞ 3፡16-17፤ ሐዋ 17፡22-23፤ 1ቆሮ 9፡19-22፤ ማቴ 9፡35-38

ጤናማ ቤተክርስቲያን ያለበትን አውድ (መልክአ ምድራዊ መገኛ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ባህል ወ.ዘ.ተ....) ከግምት ውስጥ ታስገባለች፡፡የኢየሱስ ክርስቶስ የምስራች ወንጌል የሚቀየር ሲሆን፤ ይህን የማይቀየር ወንጌል ለሰዎች የምናደርስበት መንገድ ግን ይቀየራል፡፡ የቤተክርስቲያን አባላቶች በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎች ምን እንደሚያነሳሳቸው፣ ችግራቸው፣ ህልማቸው እና እሴታቸው ምን እንደሆነ ካወቁ በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎችን በያሉበት አውድ በመድረስ ወንጌል እንዴት የእነርሱን ጥልቅ ፍላጎት እንደሚሞላ ለማስታወቅ እና ወደድህነት ለመጥራት ይረዳል

ከታች ያለው ስዕላዊ መግለጫ በአዲስ ጊዜ እና ቦታ አውዱን በጠበቀ መልኩ ወንጌልን እንዴት ማቅረብ እንደሚገባን ልናስባቸው የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን አስቀምጦልናል፡፡ ይህ ስዕላዊ መግለጫ ወንጌልን ለማድረስ ብቻ ትኩረት የሚሰጥ ሳይሆን ወንጌሉን በማዘጋጀቱ ረገድም ጠቃሚ ነው፡፡

በዚህም የእግዚአብሔርን መንግስት በቤተክርስቲያን እና በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲሰፋ ማስቻል፡፡ ቤተክርስቲያን ራሷ ያላትን ግብአት በመጠበቁ ረገድ መልካም ባላደራ መሆን ይገባታል፡፡ተቀባይነት ያለው የግብአት ባላደራ፤ ቤተክርስቲያን አባሎቿ ላላቸው ግብአት/ሃብት ማለትም ጊዜ፣ ንብረት፣ ችሎታ እና የእግዚአብሔር መቅደስ (አካላቸውን) ታማኝ ባላደራ ይሆኑ ዘንድ አጥብቃ ማሳሰብ ይገባታል፤ በዚህም የእግዚአብሔርን መንግስት በቤተክርስቲያን እና በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲሰፋ ማስቻል፡፡ ቤተክርስቲያ ራሷ ላትን ግብአት በመጠበቁ ረገድ መልካም ባላደራ መሆን ይገባታል፡፡

የመልካም ባላአደራ ምሳሌዎች፤

- ላላት ሕንፃ እና ሌሎች ቁሳቁስ አጥጋቢ በሆነ መልኩ ጥበቃ እና እንክብካቤ ማድረግ፡
  - ገንዘብን ለመቁጠር እና ለማስተዳደር የተመረጡ ዲያቆናት አሊያ ለዚሁ ተግባር የተቋቋመ ኮሚቴ እንጂ መጋቢው ገንዘብ ባያስተዳድር ይመረጣል፡፡ የሚመረጠው ኮሚቴ የሚሰበሰበውን አራት፣ የፍቅር ስጦታ እና መባ በሚገባ ይቆጥራሉ ያለምንም ስህተት መዝግበው ያስቀምጣሉ፤ ከዚያም በየጊዜው ለማህበረ ምዕመኑ ስለገንዘብ ወጪ እና ገቢ ሪፖርት ያቀርባሉ
  - ቤተክርስቲኒቱ ሰዎች ጊዜአቸውን (ቤተሰብን ለመንከባከብ፣ ለስራ፣ በቤተክርስቲያን እና በህበረሰቡ ውስጥ ግልጋሎት ለመስጠት) በአግባቡ እዲጠቀሙ ታበረታታለች፡፡
  - ቤተክርስቲያኒቱ ከራዕይዋ ጋር የሚሄድ በጀት ትመድባለች፡፡

ሕያው የሆነ ቤተክርስቲያን ሁልጊዜም ቢሆን ያለውን ግበአት በሙሉ ለአንድ አጥቢያ ከማከማቸት የሚቆጠብ እና ለሌሎች አገልሎቶች እና ተልዕኮ የሚያውል ነው፡፡ ተሳታፊዎች ቤተክርስቲያናቸው እንዴት ምዕመናን ያላቸውን ጊዜ፣ ችሎታ፣ ንብረት እና የእግዚአብሔር መቅደስ የሆነውን አካላቸውን እንዴት አድርገው መጠበቅ እዳለባቸው የምታደርገውን ጥረት ምሳሌ እንዲሰጡ ጠይቅ፡ ፡ ተሳታፊዎች ከአጠገባቸው ካለ ሰው ጋር ቤተክርስቲናቸው እንዴት ገንዘብን እንደምታስተዳድር እና ወጪና ገቢን እንደምትቆጣጠር እዲነጋሩ አድርግ፡፡

አውድን እና አውዳዊነተን ማዋሃድ፤ በተለያየ ማህበረሰብ፣ ኢኮኖሚ እና ባህላዊ አውድ ውስጥ ማለትም በተለያዩ አገራት፣ ክልሎች፣ ከተሞች፣ መንደሮች እና የቅርብ አካባቢ የሚገኝ ልዩነት ላይ ትኩረት ስጥ፡፡ እነዚህ ልዩነቶች እንዴት አድርገው የቤተክርስቲያንን ወንጌል ስርጭት፣ አምልኮ፣ አደረጃጀት፣ ራዕይ፣ ግዳጅ...የመሳሰሉት አገልሎቶቿ ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ ዘርዝር፡፡

2ጢሞ 3፡16-17፤ የእግዚአብሔር ቃል የሕይወታችን መሪ ነው፡፡ ሐዋ 17፡22-23፤ ጳውሎስ መልዕክቱ ለአካባቢው እና ለነዋሪዎቹ እንዲሆን አድርጎ አስተካክሏል፡፡ 1ቆሮ 9፡10-22፤ ጳውሎስ ሰዎች የወንጌል መልዕክቱን ይረዱትና ይቀበሉት ዘንድ ራሱን ከእነርሱ ጋር አዛምዶ ነበር፡

ማቴ 9፡35-38፤ ኢየሱስ ሰዎችን ባሉበት ስፍራ ፈልጎ ያገኛቸው ዘንድ ካለበት ስፍራ እነርሱ ወዳሉበት ይሄድ ነበር፡፡



መቀበል ማስተካከል መፍጠር መለወጥ መቃወም

የራስ ማድረግ መገልበጥ አዲስ መቀየር

መልመጃ፤ የቤተክርስቲያናችሁን ጤናማነት መዝኑ

- ማህበረሰባችን ያለበትን አውድና ችግር ቤተክርስቲያናችን በሚገባ ተረድታዋለች፡፡

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

- ከማህበረሰቡ ጋር ህብረትን ለማጠናከር ቤተክርስቲያናችን ከፍተኛ ጥረት ታደርጋለች

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

**ማጠቃለያ**

እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የራሱ የሆነ ልዩ ማንነት እና ችሎታ አለው፡፡ በተነጋገርንባቸው አምስቱ የቤተክርስቲያን ተግባራት ላይ ውጤታማ የሆነ ቤተክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ በመንፈስ ቀዱስ በመመራት በማህበረሰቡ ውስጥ ለውጥ ያመጣል፡፡ ሰዎች በክርስቶስ አዲስ ሕይወት እንዲያገኙ የሚጋብዝና በእርሱ(እግዚአብሔር) ውስጥ በመኖር ለእርሱ ክብርን እንዲያመጡ ያስችላል፡፡

አማራጭ ተግባር፤ ተሳታፊዎች ከአምስቱ የቤተክርስቲያን እድገት አቅጣጫዎች ቤተክርስቲያናቸው ጠንካራ የሆነባቸውን እና በየትኞቹ ደካማ እንደሆነች እንዲያስቡ አበረታታቸው፡፡ ከዚያም 3 ወይንም 4 ሆነው አንዳቸው ለሌላቸው እዲነግሩ አድርግ፡፡ በመጨረሻም ከእነዚህ ውስጥ አንዱን በማንሳት እንዴት ሊሰሩበት እንደሚችሉ አነቃቂ ውይይት እዲያደርጉ ጠይቃቸው፡፡

## ማስታወሻ


# ክፍለትምህርት 3

# አምስቱ የጤናማ ቤተክርስቲያን ተግባራት

### *መግቢያ*

ክፍለትምህርት 3 ስለ አምስቱ የጤናማ ቤተክርስቲያን ተግባራት በዝርዝር ያስቀምጥልናል፤ እነርሱም፡- ወንጌል ስርጭት፣ ደቀመዝሙር ማድረግ፣ ግልጋሎት፣ ህብረት እና አምልኮ ናቸው፡፡ በእነዚህ መስፈርቶች ያለንበትን ቤተክርስቲያን ከተመዘነ፤ የቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች ለሚያዘጋጁት ስልታዊ ዕቅድ እንደ ግብአት ያገለግላል፡፡

አምስቱ መሰረታዊ ተግባራት፤ ሐዋ 2፡24-27




እያንዳንዱ ተግባር በሌሎቹ ተግባር ላይ ተፅዕኖውን ያሳርፋል፡፡

1. አሳማኝ ምስክርነት፤ ሐዋ 2፡47፤ 2ጢሞ 4፡1-2፤ ሐዋ 5፡42፤ ቆላ 1፡28-29

ቤተክርስቲያን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቲስን ወንጌል በቃል እና በተግባር በመንገርና በመኖር ሰዎች የእግዚአብሔር መንግስት አካል ይሆኑ ዘንድ ሰውን ሁሉ ትጋብዛለች፡፡ ሰዎች መልካሙን የምስራች ያምኑ ዘንድ፣ ሕይወታቸውን ለኢየሱስ እንዲሰጡ እና የእርሱ ደቀመዝሙር እንዲሆኑ ሰዎችን ይጋብዛል፡፡ ሕይወታችን በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆናችንን ይመሰክራል፤ እግዚአብሔር ለሰራው ስራ "ሕያው ምስክር" ይሆናሉ፡፡

እግዚአብሔር ነው ለቤተክርስቲያን የሚጨምረው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ልብ ውስጥ በመስራት በክርስቶስ የተሰጠውን ህይወት እንዲቀበሉ ያንቀሳቅሳቸዋል፡፡

ሐሳብን ለማንጸባረቅ የቀረቡ ጥያቄዎች፡-

- ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ለምን ያህል ሰው ወንጌል ሰብኬአለሁ?
- ቤተክርስቲያናችን ለምንያህል አማኞች እምነታቸውን ማካፈል የሚያስችላቸው ስልጠና ሰትታለች?

ሰዎች ወደክርስቶስ ይመጡ ዘንድ የሚያስፈልጋቸው ሶስት አይነት ለውጦች፡-

1. የኃይል ለውጥ፤ ሰዎች የራሳቸውን ድካም በመገንዘብ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚሰራውን ሕይወት የሚሰጣቸውን፣ በህይወታቸው ያለውን የኃጢአት ኃይል የሚሰብረውን እና የምንፈስን ፍሬ ማለትም ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ትህትና፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋሃት እና ራስን መግዛት በሕይወታቸው የሚያመጣውን የእግዚአብሔርን ኀይል መለማመድ መጀመር፡፡

2. የእምነት ለውጥ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው የሆነ፤ ከሙታን የተነሳ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለማመን የሰዎች አይን ተከፍቷል፡፡ ሰዎች እግዚአብሔር በቃሉ (በመጽሐፍ ቅዱስ) አንደሚናገር እንዲገነዘቡ እና የሚናገረውም እውነት እንደሆነ እና ሊከተሉት የሚችል አንደሆነ ያውቃሉ፡፡

3. የፈቃድ ለውጥ፤ ሰዎች ሕይወታችን ለክርስቶስ በመስጠት ሁሉንም የህይወታቸውን ክፍል ለእርሱ ፈቃድ ማስገዛት ይኖርባቸዋል፡፡

መልመጃ፤ የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት መዝን

እያንዳንዱን አርፍተነገር በማንበብ ሐሳብህን አመላክት ("1" ከአርፍተነገሩ ጋር ሙሉ ለሙሉ እንደማትስማማ ያሳያል፤ "10" መሉለሙሉ እንደምትስማሙ ያመላክታል፡፡)

- ቤተክርስቲያናችን አባላቶቿ ማህበረሰቡን በወንጌል እንዲደርሱ ታሰለጥናለች ታስታጥቃለች

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

- የቤተክርስቲያኖችን አባላት በሚያደርጉት የወንጌል ስራ ውስጥ ተሳታፊ ነኝ

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

ከቤተክርስቲያን መሪዎችህ ጋር የምታደርገው ክትትል፡-

- አንዴት ነው ቤተክርስቲያናችን ሰዎች የእግዚአብሔርን ኃይል እንዲያዩ፣ የእርሱን እውነት እንዲሰሙ እና ለክርስቶስም በሙሉ ልብ በመሰጠት ምላሽ እንዲሰጡ የምታበረታታው?

2. ሁሉን አቀፍ የደቀመዝሙርነት ስልጠና፤ ሐዋ 2፡42፤ ማቴ 28፡ 18-20፤ 2ጴጥ 3፡18

ጤናማ ቤተክርስቲያን በየትኛውም የእድሜ ደረጃ ያሉ ሰዎች ክርስቶስንና የእርሱን ፈቃድ በበለጠ እንዲያውቁ እና በማንኛውም የሕወት አቅጣጫቸውና በዕለት ተዕለት ሕወታቸው እርሱን እንዲከተሉ ትረዳለች፡፡ እርሱን እና የእርሱን ፈቃድ በበለጠ ባወቅንና በመንፈሱ በተደገፍን ቁጥር በኑሮአችን በበለጠ ክርስቶስን እየመሰልን እንሄዳለን፡-

1. ስነስርአት/conduct


2. አስተሳሰብ

3. ባህርይ

4. መስጠት

ስዕላዊ መግለጫ፤ የተከፋፈለ እምነት ከ ሁሉን አቀፍ እምነት




የተከፋፈለ እምነት ሁሉን አቀፍ እምነት

መልመጃ፤ የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት መዝን

- አንድ ሰው ወደ ጌታ ሲመጣ ወዲያው ደቀመዝሙር ያደርገው ዘንድ አንድ ሰው ይመደብለታል

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

- ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወት እንዳድግ ረድታኛለች

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

ከቤተክርስቲያንህ መሪዎች ጋር የምታደርገው ክትትል፡-

የተሟላ ደቀመዝሙርነት፤

- አቋም (ባህሪያችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ኢየሱስን እየመሰለ ይሄዳል፤ ፊሊ 1፡27፤ ኤፌ 5፡1-2)
- አስተሳሰብ (እኛ የክርስቶስ ልብ አለን፤ ፊሊ 2፡5፤ ፊሊ 4፡8)
- ባህሪ (የመንፈስን ፍሬዎች በሕይወታችን እናንጸባርቃለን፤ ገላ 5፡22-24፤ ኤፌ 5፡1-2)
- መስጠት (የሚያስከፍለን ዋጋ ምንም ይሁን ምን ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንሰጣለን፤ ማቴ 26፡39፤ ዮሐ 6፡38)

የተከፋፈለ እምነት፤ እምነት የሕይወታችን ሌላው ገጽታ ነው፡፡ በአምልኮ ጊዜ እግዚአብሔርን እናስብ እና ከአምልኮ ቀን ውጪ ያሉት ቀናትን የምናሳልፈው ስለእርሱ ሳናስብ ሊሆን ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ከቤተሰብ ሕይወታችን፣ ከገንዘባችን፣ የፖለቲካ አቋማችን እና አካል ብቃት እንቅስቃሴአችን ወ.ዘ.ተ… ጋር እንዴት እንደሚመለከተው ትኩረት ሰጥተን አናስበውም፡፡

ሁሉን ያዋደደ እምነት፤ በኢየሱስ ላይ ያለን እምነት ለቤተሰባችን የሚኖረንን አመለካከት፣ በማህበረሰባችን እና በአገራችን እንዴት መኖር እዳለብን፣ እንዴት አድርገን በሰፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መጫወት እንዳለብን፣ እንዴት አድርገን ገንዘባችንን ማስተደዳር ወ.ዘ.ተ…ላይ ተጽዕኖውን ያሳድራል፡፡ በእያንዳንዱ የሕይወት ክፍላችን እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንጥራለን፡

- እንዴት ነው ቤተክርስቲያናችን ሰዎች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባላቸው ህብረት እንዲያድጉ የምታግዘው?
- ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያጠኑ እና በህይወታቸው እንዲተገብሩ ቤተክርስቲያን ምን አይነት እድሎችን ታዘጋጃለች?
- ሰዎች በጋራ ወይንም አንዳቸው ለሌላቸው አንዲጸልዩ ቤተክርስቲያን ምን ኤንት እድሎችን ትፈጥራለች?
- አባላት በቤተሰብ ሕይወታቸው፣ በሚወስኑት ውሳኔ፣ በዘወትር ስራቸው፣ በገንዘብ አጠቃቀማቸው እና በጊዜ አጠቃቀማቸው ኢየሱስን መከተል እንዲማሩ በምን መልኩ ታግዛቸዋለች?

3. የርህራሄ አገልግሎት፤ ሐዋ 2፡45-46፤ ገላ 6፡10፤ ማር 12፡31፤ ያዕ 2፡17

ቤተክርስቲያን የሰዎች እና የማህበረሰብን ፍላጎት በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ለመሙላት እና የእርሱ ደቀመዝሙር ይሆኑ ዘንድ ቤተክርስቲያን ሁለንተናዊ የሆነ እገዛ ታደርጋለች፡፡

የያዕቆብ መጽሐፍ በግልጥ እንደሚያስተምረን ከስራ የተለየ ዕምነት የሞተ እንደሆነ ነው (ያዕ 2፡17)፡፡ ሌሎችን የምናገለግለው ድህነትን ለማግኘት ሳይሆን እግዚአብሔር ለእኛ ካደረገልን ውለታ አክብሮት ተነስተን ነው፡፡

በተሰጠን ጸጋ እና ባለን ሃብት ሌሎችን ማገልገል የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች የምናረጋግጥበት መንገድ ነው፡፡

በግልጋሎት እና በወንጌል ስርጭት መካከል ያለ ትስስር

1. ግልጋሎት የወንጌል ስርጭት ውጤት ነው፡- የእግዚአብሔር ፍቅር ለሌሎች ግልጋሎት እንድንሰጥ ያደርገናል፡፡

2. ግልጋሎት ለወንጌል ስርጭት እንደ ድልድይ ያገለግላል፡- በቅድሚያ ጠንካራ የሆነ ግልጋሎትን የሚያስረዱ ተግባራት እንከውናለን፤ እናም እነዚህ የግልጋሎት ተግባራት እምነታችንን ለሰዎች የምናካፍልበት በር ይከፍትልናል፡፡

3. ግልጋሎት የወንጌል ስርጭት አጋቢ ነው፡- ሌሎችን ስናገለግል፤ እግዚአብሔር ለእነርሱ ስላለው ፍቅር እንናገራለን፡፡

መልመጃ፤ የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት መዝን

- ቤተክርስቲያናችን የሰዎችን አካላዊ ፍላጎት ለማሟላት እርዳታ ታደርጋለች

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|

- በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ፍቅር በተግባር ለማሳየት እንደምንፈልግ ያውቃሉ

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|

ከቤተክርስቲያን መሪዎችህ ጋር ክትትል አድርግ፡-

- እንዴት የቤተክርስቲያናችን አባሎች በማህበረሰቡ ውስጥ ግልጋሎት ይሰጣሉ?
- አንዴት ነው ጉባኤያቸን በሙሉ/በአንድነት ማህበረሰቡን ማገልገል የሚችለው?

4. ተንከባካቢ እና አቃፊ ማህበረሰብ፤ ሐዋ 2፡42፣ 44፣ 46፤ ገላ 6፡ 2፤ ኤፌ 4፡25-26 እና 5፡2

በጤናማ ቤተክርስቲያን ውስጥ አባላት አንዳቸው የሌላቸውን ሸክም መሸክምን እንደሙሉ ደስታ የሚቆጥሩት ሲሆን በዚህም የእግዚአብሔርን በርህራሄ የተሞላ ፍቅር ያሳያሉ፡፡ ይህም ማለት እኛም አንዳችን የሌላችንን ሸክም መሸከም ትክክለኛ በሆነ መንገድ ለማግኘት እንችል ዘንድ በሚገባ መተዋወቅ ያስፈልገናል፡፡ የግሪክ "ኮይኖኒያ" የሚለው ቃል ፍቺ "በጋራ" የሚል ትርጓሜ ነው ያለው፡፡ የክርስቲያን ህብረትም በቅድሚያ ክርስቶስ ማዕከላዊ እና የጋራ ሆኖ የሚጀመርና በዚህም በክርስቶስ ወንድም እና እህቶቻችን ከሆኑ ሰዎች ጋር ማን እንደሆንን ማስረዳት እና ያለንንም ማካፈል ይኖርብናል፡፡ አነስተኛ የሰው ቁጥር ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ክርስቲያኖች እንዲረዳዱ እና በእምነታቸውም በህብረት እንዲያድጉ ይረዳል፡፡

ጤናማ ቤተክርስቲያን ግጭት በአንድ ጉባኤ ውስጥ መፈጠር አንዱ የሕይወት አካል እንደሆነ ይገነዘባል፡፡ ለሚገጥማቸው ችግር መፍትሄ ለመስጠት በጉዳዩ ላይ ትኩረት በማድረግ ገንቢ በሆነ መንገድ ችግሩን ለመፍታት የሚሄዱበት መንገድ ለቤተክርስቲያን ራዕይ ታማኝ የሆነ እና እውነትን በፍቅር በመናገር ነው፡፡ መሪዎች ምንም እንኳን በፍቅርና አክብሮት የተሞሉ መሆን ቢገባም ጥብቅ መሆንም የዛኑ ያህል አስፈላጊ ነው፡፡ አባላት ወይንም መሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ መርህ ለመሄድ ፈቃደኛ አልሆን ካሉ፤ በፍቅር ሊስተካከሉ የሚገባ ቢታመንም ጠንከራ የሆነ አያያዝ አስፈላጊ እንደሆነ እሙን ነው፡፡

ሀ. ዮሐ 17፤ የህብረት ስነመለኮት የመነጨው በቀጥታ ከስሉስ አሃድ ከሆነው ከእግዚአብሔር ከራሱ ነው- የመጀመሪያው ህብረት፡፡

ለ. መዝ 133፤ በብሉይ ኪዳን አስቀድሞ በአማኞች መካከል የሚኖር የህብረትን ዋጋ ዘግቦልናል፡፡

መልመጃ፤ የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት መዝን

ተንከባካቢ እና አቃፊ ማህበረሰብ፤ በመገለል፣ ብቸኝነት፣ መለያየት እና ቀውስ በተሞላች ዓለም፤ ቤተክርስያን አፍቃሪ፣ ታራቂ፣ በጸጋ የተሞላ እና ይቅርባይ ማህበረሰብ ቤተክርስቲያን ማዘጋጀቷ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

ተሳታፊዎች እርስበእርስ መተዋወቅ እና መረዳዳት የሚችሉበት ሌላ መንግድ ይኖራቸው እንድንሆን ጠይቅ፡

እንዴት ነው መሪዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚፈጠርን አለመግባባት የሚፈቱት፤

1. ችግሩን መለየት ምንድን ነው ለሰዎች ያለመግባባት ምንጭ እየሆነ ያለው፡፡)
2. የተፈጠረውን አለመግባባትን በተቻለመጠን ነጥሎ መተንተን፤ መንስኤውን፣ አለመግባባቱን ያባባሰውን ባህርይ፣ የመሳሰሉትን ማጥናት፡፡ ሰዎች አንዳቸው ሌላቸውን በቃላት እንዲያጠቁ ከማድረግ ይልቅ ባህርይ ላይ አተኩሮ መስራት፡፡
3. አለመግባባት ውስጥ የገቡ ሰዎች የሚጋሩት አሳብ እዳለ መፈለግ እና ማሳየት፡፡
4. አለመግባባቱ የሚፈታበትን መንገድ መፈለግ፡፡
5. አለመግባባቱን ለመፍታት የምንጠቀምበት መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ለተቀመጠልን ለእግዚአብሔር ሕግ የታመነ፣ ለቤተክርስቲያኒቱ ራዕይ እና ተልዕኮ የታመነ እና ለተፈጠረው ሁኔታ ተገቢ መሆን ይኖርበታል፡፡
6. ሰዎች ይቅርታ እንዲጠይቁ እና ይቅር እንዲሉ አበረታታ፡፡
7. ውሳኔህን በተግባር አሳይ፡፡

- የቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት ምዕመናን በአካባቢያቸው ካሉ ሰዎች ጋር መልካም ህብረት

እንዲኖራቸው ያግዛል

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

- በቤተክርስቲያናችን አዎንታዊ የሆነ ህብረት አለ

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

ከቤተክርስቲያን መሪዎችህ ጋር ክትትል አድርግ፡-

- በቤተክርስቲያናችን ያሉ በክርስቶስ ወንድሞች እና እህቶች የሆኑ አባላት ምን ያህል ይተዋወቃሉ?
- እንዴት ባለ መልኩ ነው አንዳቸው ሌላኛቸውን ሲረዱ የምንመለከተው?
- ቤተክርስቲያናችን ግጭትን የምትፈታበት የተለየ መንገድ አላት?
- በቤተክርስቲያናችን ለመጨረሻ ጊዜ የተፈጠረ አለመግባባት ምንድን ነው፤ እንዴትስ ተፈታ?

5. ተንቀሳቃሽ አምልኮና ጸሎት፤ ሐዋ 2፡42፣ 42፣ 47፤ መዝ 47፡1፤ መዝ 48፡9፤ ሮሜ 12፡1-2

ቤተክርስቲያን እንደእግዚአብሔር ቤተሰብ ተሰባስበው ከእርሱ ለመስማት እና በአምልኮአቸው፣ በኑዛዜአቸው፣ በምስጋናቸውና ምልጃቸው ለእርሱ ምላሽ የሚሰጡበት ስብስብ ነው፡፡ በአምልኮ ለእግዚአብሔርን ታላቅነት እውቅና በመስጠት ራሳችንን ለእርሱ እናስገዛለን፡፡

የአምልኮ አገልግሎት የሚካሄድበት ጊዜ፤ እግዚአብሔር እና ህዝቡ የሚገናኙበት ስለሆነ የተለየ ነው፡፡ ይህ የተለየ ጊዜ ደግሞ ሰዎች ለእግዚአብሔር ንግግራቸውን የሚያሰሙበት እግዚአብሔርም ሰዎችን የሚናገርበት ነው፡፡

- እግዚአብሔር የጠራን እንድናመልከው ነው፤ እኛም ለጠራን ጥሪ ምላሽ የምንሰጠው በአንድነት ሆነን እርሱን በመባረክ ነው፡፡
- እግዚአብሔር የጠራን ኃጢአታችንን እንድንናዘዝ ነው፤ እኛም ለዚህ ጥሪ ምላሽ የምንሰጠው ኃጠአታችንን በመናዘዝ እና ምህረትን በመጠየቅ ነው፤ እግዚአብሔርም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ይቅር ይለናል፡፡
- እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ይናገረናል፤ እኛም ለሚናገረን ቃል እምነት፣ የፍቅር ስጦታ፣ ምስክርነት እና የምልጃ ጸሎት በማድረግ ይሆናል፡፡
- እግዚአብሔር ፍቅሩን አእማድ ባልናቸው የቤተክርስቲያን ስርአቶች (ጥምቀት እና የጌታ እራት) አሳይቶናል- እኛም እግዚአብሔርን ስራ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ተቀብለናል፡፡
- እግዚአብሔር ባርኮ በዓለም ላይ ሁሉ እንደርስ ዘንድ ልኮናል- እኛም የአምልኮ ጊዜአችንን ጨርሰን ወደየተግባራችን ስንሰማራ እግዚአብሔርን በኑሮአችን ልናገለግለው ተዘጋጅተን ነው፡ ፡ የሮሜ 12 የመጀመሪያው ቁጥር አምልኮ ሰፋ ያለ ትርጉሙ የህይወትን ሁለንተናዊ አቅጣጫ

የሚይዝ እንደሆነ ያመላክተናል፡፡ ዘመናችንን ሁሉ ስለእርሱ መልካምነት እና ታላቅነት በእግዚአብሔር መገኘት እንኖራለን፡፡

ቤተክርስቲያን እንድታድግ የሚያግዙ የአምለኮ ምክንያቶች፡-

1. ለእንግዶች ሞቅ ያለ ሰላምታ (እነዚህ እንግዶች የተመቸ ስፍራ አንዳገኙ ማረጋገጥ/ ድንገት በመካሄድ ላይ ያለው ፕሮግራም ግር የሚላቸው ነገር ካለ ማብራራት)፡፡

2. አዳዲስ ሰዎችን መከታተል (አዳዲስ ሰዎች በመጡ በጥቂት ጊዜ በግል እነርሱን ማወቅ)፡፡

3. በአምልኮ አካባቢ ለአዳዲስ ሰዎች ስፍራ መስጠት፡፡

4. ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ያለው ስብከት ለቃለ እግዚአብሔር ታማኝ የሆነ እና ለሰዎች ሕይወትም ትርጉም ያለው ለውጥ የሚያመጣ ነው፡፡

5. ሰዎች በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ የሚያውቁበት ግልጥ የሆነ መንገድ/አሰራር አለ፡፡

ትንተና፤ አምስት ተግባራት

ተሳታፊዎች በምስሉ ላይ የተመለከተውን ቅጽ ከሞሉ በኋላ፤ ቤተክርስቲያናቸው በየትኛው ግዳጅ ላይ ጠንካራ ናት በየትኞቹስ ላይ ደካማ ናት፡፡ ይህን ውጤት አጠገባቸው ላሉ ወይንም ከ3-4 ሰዎች ያሉት ቡድን በማደራጀት ለቡድናቸው እዲናገሩ አድርግ፡፡ ጊዜ የሚበቃችሁ ከሆነ ተሳታፊዎች እንዴት አድርገው ደካማ የሆነውን የቤተክርስቲያን ተግባር ሊያሻሽሉ እንደሚችሉ እንዲወያዩ አድርግ፡፡

መሪዎች ውሳኔ በሚያሳልፉበት ወቅት በቤተከርስቲያኒቱ እድገት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸውን ጉዳዮች ማለትም አደረጃጀት፣ መርሃ ግብር/ፕሮግራምና ተግባቦት እና ቤተክርስቲያን ራሷን ያገኘችበትን መንፈስና የማህበረሰብ አውድ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹን በክፍለትምህርት 4 እንመለከታቸዋል፡፡

መልመጃ፤ የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት መዝን

- በቤተክርስቲያናችን የሚካሄድ አምልኮ የክርስትና ሕይወታችንን ያሳድጋል ያጎለብታል

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

- በአምልኳችን ስሉስ-አሃድ የሆነው ማለትም አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ይወደሳል

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

ከቤተክርስቲያን መሪዎችህ ጋር በመሆን ክትትል አድርግ፡-

- አምልኮአችን ትርጉም የሚሰጥ እና በደስታ የተሞላ ነው?
- ጥበብን ለእግዚአብሔር ክብር እንጠቀምበታለን?
- በእነዚህ (ሙዚቃ፣ ተለይተው የሚታወቁ መሪዎች፣ ወ.ዘ.ተ…) ጉዳዮች ላይ ከመጠን ያለፈ ትኩረት እንሰጣለን?

## ማጠቃለያ

ከአምስቱ ግዴታዎች መተጨማሪ በእነዚህ አምስት ተግባራት ጠንካራ የሆነች ቤተክርስቲያን ጤናማ ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰቡ ስላለችበት እውነት ብርሃን ፈንጣቂ ትሆናለች፡፡

ትንተና፤ አምስት ተግባራት
ለእያንዳንዱ ተግባራት የሚሆኑ የቤተክርስቲያናችሁን አገልግሎቶች አመላክቱ፡-

| ወንጌል ስርጭት | ደቀመዝሙር | ግልጋሎት | ህብረት | አምልኮ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

1. ከላይ ያለውን ሰንጠረዥ ከሞላችሁ በኋላ የተዘረዘሩት ዘርፎች ጥንካሬ እና ድካም ምንድን ነው?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

2. የሞላቹትን ሰንጠረዥ ሁሉንም አገልግሎቶች ለመቅረብ አማካይ ነው?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

# ክፍለትምህርት 4

# ለዋጩ ስርአት

### *መግቢያ*

ከህክምና እና ከሳይንስ ጥናት ማህበረሰብ ስለጥቃቅን ነፍሳት (ሕይወት ስላላቸው ነገሮች) እንደ ስርአት በማስቀመጥ ያስተምሩናል- ሙሉ አካል የሚባለው ብዙ ስርአቶች ከውስጥም ከውጭም ተደማምረው የሚሰሩት ነው፡፡ በጥቃቅን የሰውነት ስርአት ውስጥ የሚሰራው ለታላላቅ የአካል ክፍሎች ስርአትም ይሰራል፡፡

የጫካ እና ዛፎቹ ምሳሌ፤ በትክክል ለማገልገል የቤተክርስቲያን መሪዎች ስለእያዳንዱ የአገልግሎት ዘርፍ (ዛፎች) ብቻ ሳይሆን ስለጠቅላላ የአገልግሎ ዘርፎች ድምር ውጤት (ጫካ) ጠንቅቀው መረዳት ያስፈልጋቸዋል፡፡

ቤተክርስቲያን ሕያው የሆነች አካል ናት- የክርስቶስ አካል- እንዲሁም ድርጅት ናት፡፡ እንደውም ውስብስብ እና የተለያዩ ንዑስ ክፍሎች ያሉት አካል፤ ከአንድ የተወሰነ ከባቢ ጋር መስተጋብር ያለው ነው፡፡ አንዱን ስርአት የፈጠሩት ስርአቶች አንዳቸው በሌላቸው ላይ ጥገኛ የሆኑ እና አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ህብረት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህ ትልቅ ስርአት ከሌሎች ስርአቶች ጋር በጋራ ተግባርን ይከውናል ደግሞም ለሌሎች ተግባር ምላሽ ይሰጣል፡፡ አንዱ ከሌላው ጋር በመደጋገፍ የሚፈጥሩት ህብረት እና መስተጋብር ስርአት አስፍተን የምንመለከትበት የዕይታ አድማስ "ክፍት ስርአት" ይባላል፡፡ ይህ ጽንሰሐሳብ ሊተገበር የሚችል እና ጤናማ የሆነ "ደቀመዝሙር ማድረግ" የሚቻልበትን በዚህም ይህን ተግባር የምናስቀጥልበትን መንገድ አንድናገኝ እና ተልዕኮ ተኮር የሆነ ማህበረምዕመን በመሆን አስፈላጊውን ለውጥ ማድረግ እንድንችል ይረዳናል፡፡




ዛፉን እንደምትመለከት ሁሉ ጫካውንም መመልከት ይኖርብሃል

መርህ፤ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደመሆኗ ሕያው አካል ናት፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የምትኖረው በጸና፣ እግዚአብሔር በዓለም ለመስራት የሚጠቀምበት ግልጥና ተጨባጭ በሆነ ድርጅት (ማህበረምዕመን፤ ቤተዕምነት) ነው፡፡ አንድ ድርጅት እንዴት እንደሚሰራ በተረዳን ቁጥር ማህበረምዕመናችን ውጤታማ ተግባራትን እንዲከውን መርዳት እንችላለን፡፡

መልመጃ፤ የተበታተኑ ቁጥሮች

በ30 ሰከንድ ውስጥ እነዚህ የተበታተኑ ቁጥሮችን (ከ1 ጀምራችሁ) በቅደም ተከተላቸው መሰረት አስፍሩ፡፡ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ምን ያህል ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸው መደርደር እንደምትችል አስረዳ፡፡ 1ን ስታይ ማክበብ 2ን ስታይ ማክበብ... እንዲህ እያልክ መቀጠል፡፡

በዚህ ክፍት ስፍራ ላይ ካከበብካቸው ከፍተኛውን ቁጥር አስፍር______________




ይህ የሚያመለክተው፡-

- ትርጉም ያለው ቅርጽ
- ቅደም ተከተል
- ውጤታማነት
- ንድፍ
- የድርጅትን የትግበራ እቅድ መረዳት

ልክ 30 ሰከንዱ ሲያበቃ ተሳታፊዎች የደረሱበትን ትልቅ ቁጥር እንዲጽፉ አድርግ፡፡ ከዚያም ሁለተኛውን የመልመጃውን ክፍል ቀጥል፤ በዚህ ጊዜ ተሳታፊዎች ቀድመው የሰሩትን መልመጃ (ምን ያህል ቁጥሮችን በ30 ሰከንድ ማክበብ እንደሚችሉ) ደግመው እንዲሞክሩ አድርግ፤ በዚህ ወቅት ተግባሩን ከመከወናቸው በፊት ከዚህ በታች የቀረቡትን ሁለት ፍንጮች ንገራቸው፡-

ሀ. ቁጥሮቹ በአራት ቦታ የተከፈሉ ናቸው፤ ከ1-6 ያሉት ቁጥሮች የሚገኙት በላይኛው አጋማሽ ላይ ሲሆን ቀጣዮቹ ስድት ቁጥሮች ማለትም (ከ7-10) በታችኛው ግመሽ ነው የሚገኘው፡፡ ቀጣዮቹ ስድስት ቁጥሮች ደግሞ ማለትም (ከ13-18) የሚገኙት ደግሞ በላይኛው አጋሽማሽ ላይ ነው፡፡ ቀጣዮቹ ስድስት ቁጥሮች (19-23) ደግሞ በታችኛው አጋማሽ እንዲህ …እንዲህ እያለ ይቀጥላል፡፡

ለ. ሌላው ልብ ልንለው የሚገባን ሁለት ተከታታይ ቁጥሮች በአንድ ሩብ ክፋይ ውስጥ አይገኙም፡፡ ለምሳሌ፤ ከአንድ ከ1-6 የሚገኙት ቁጥሮች በላይኛው አጋማሽ በሚገኙ ክፋዮች በቀኝና በግራ በየተራ መገኘታቸውን ማስተዋል ነው፡፡

እነዚህን ሁለት ፍንጮች ከሰጠህ በኋላ ተሳታፊዎች ተግባሩን ደግመው እንዲከውኑ፤ በ30 ሰከንድ ውስጥ የሚችሉትን ያህል ቁጥር በቅደም ተከተል እንዲያከብቡ አድርግ፡፡ ይህን ከተገበሩ በኋላ ከመጀመሪያው የበለጠ ቁጥር ማከበብ የቻሉ ተሳታፊዎች እጃቸውን በማውጣት እንዲናገሩ አድርግ፡፡ በዚህ ጊዜ ከሞላ ጎደል ተሳታፊው ሁሉ ከፍተኛ ቁጥር ያስመዘግባል፡፡ ተሳታፊዎች በሁለተኛው ተግባር ለምን ከፍተኛ ቁጥር ማስመዝገብ እንደቻሉ ጠይቅ፡፡ ተሳታፊዎችም እንዲህ ብለው ሊመልሱልህ ይችላሉ፤ በዚህ ጊዜ አሰራሩን ስላወቅነው ወይንም ቁጥሮቹ የት የት እንደሚገኙ ስላወቅን፡፡

የዚህ ተግባር ዓላማ አንድን ስርአት አደረጃጀት ማወቅ ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው ማሳየት ነው፡፡ በተመሳሳይ ቤተክርስቲያናት እንዴት እንዳደረጉ መረዳት እግዚአብሔር በሰጠን አገልግሎት በበለጠ ውጤታማ እንድንሆን ያደርገናል፡፡

## የአንድ ድርጅት ግብአቶች

ስዕላዊ መግለጫ 1፤ በአንድ ማህበረምዕመን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳደሩ ውጫዊ ሁኔታዎች

የአንድ ድርጅት ይዘቶች፤ መለኪያ/መድረሻ

እነዚህ አንድን ድርጅት ከሌላው የሚለዩ ውጫዊ መዳረሻዎች ናቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እሴቶች፣ የእኛ የምለው ኃይማኖታዊ ወግ እና የድርጅታችን ታሪክና እሴት ማን እንደሆነ እና ምን ልንሰራ እንደምንችል ይገልጣሉ፡፡


ለምሳሌ አንድ ጤናማ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገደብን የሚከተል ከሆነ አባቶቹ በሃሜት ይገኙ ዘንድ አይፈቅድም (ዘሌ 19፡ 16፤ መዝ 34፡13፤ ያዕ 4፡11)፡፡ ገደብ እንደ ቤተክርስቲያን ሕንፃ እና ግብአት የመሳሰሉ ቁሳዊ ነገሮችንም ይመለከታል፡፡

- አንዳንድ አብሮ ሰራተኞች ልንደራደራቸው እና አሳባቸውን ሊቀይሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ባህላዊ ልምምዶችና የማህበረምዕመን ልምድ ሊቀየር ይችላል፡፡ ኃይማኖታዊ ወጎች በተለያየ መንገድ ሊለወጡ ይችላሉ፤ ልክ እዲሁ እሴቶቻችንም እግዚአብሔር ከጠራን ጥሪ ጋር የተስማማ እድገት ካለን እሴታችንም ሊቀየር ይችላል፡፡

አንዳንድ መለኪያዎች የምንደራደርባቸው ሳይሆኑ ቁርጥ ያለ ውሳኔ ተላልፎባቸው የተቀመጡና ያለማቅማማት የምንቀበላቸው ናቸው!

ማህበረሰብ፤ ከባቢ

ኃይማኖታዊ ስርዓቶች፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እሴቶች




ድርጅት ተኮር ታሪክ

ማዕከላዊ የአገልግሎት እሴት

- አንዳንድ ውጫዊ ተጽዕኖ አምጪ ሁኔታዎች የምንደራደራቸው እና በቀላሉ ሊለወጡ የሚችሉ ናቸው፡፡
- አንዳንዶች ተጽዕኖ አምጪ ሁኔታዎች የምንደራደራቸው አይደሉም፤ ቋሚ ናቸው፡፡

ተግባር፡-

አውድ፤ እያንዳንዱ ድርጅት በአንድ የተለየ ሁኔታ ውስጥ ይኖራል፡፡ እያንዳንዱም ማህበረምዕመን በተወሰነ ጊዜ እና በተወሰነ ቦታ ራሱን ያገኛል፡፡ አካባቢያችንን (ባህላችንን፣ የሰዎችን የአኗኗር ዘይቤና የመሳሰሉትን…) በሚገባ ማወቅ ወንጌልን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማድረስ ያስችለናል፡፡

የክትትል ተግባራት፤ መሪዎች በቤተክርስቲናችሁ ቅርብ አካባቢ ስላሉ ሰዎች የሚያውቁትን (ዝንባሌአቸውን፣ ፍላጎታቸውን ወ.ዘ.ተ…) ሁሉ ዘርዝረው እንዲጽፉ አድርግ፡፡ የቅርብ አካባቢ ሰዎችን ቃለመጠይቅ በማድረግ ስለራሳቸው እና ስለቤተክርስቲያን ስላላቸው አመለካከት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡

በቤተክርስቲያናችሁ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር ውጫዊ ሁኔታ ውስጥ አንድ ምሳሌ የሚሆንህን ተናገር፡፡ ልትደራደሩ የምትችሉት ነው ውስን ቋሚ ነው?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

ከቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር ክትትል አድርግ፡-

- በቤተክርስቲያን አባላቶችህ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር እና ቅርጽ የሚለውጡ ውጫዊ ሁኔታዎች ውስጥ ጥቂቱን ለይተህ አሳይ፡፡ የትኞቹ በበለጠ የምንደራደርባቸው ናቸው? የትኞቹስ የማይለወጡ ናቸው?

ማስታወሻ፤ ይህኛው ከሰርቶ ማሳያው በጣም ውስብስብ የሚባለው ነው፡፡ ምናልባት በዚህ የቀረቡት ስዕላዊ መግለጫዎች ምንም አይነት ስሜት የሚሰጡ እና ለመረዳት ሚከብዱ ከሆነ፤ በተሳታፊዎች ማኑዋል ውስጥ ገጽ 28 ላይ ወደሚገኘው "ቀዩ ምንጣፍ" ወደሚለው ትምህርት በቀጥታ መሻገር ትችላለህ፡፡


የአንድ ስርአት ቁልፍ ጽንሰ-አሳቦች፤ አንድ ድርጅት ውስጣዊ እና ውጫዊ ግብአቶች አሉት፡፡ እንደ ድርጅት የተዋቀሩ ቤተክርስቲያናት በግለሰብና ማህበረሰብን ለመለወጥ እና እግዚአብሔርን ለማክበር በዚህም የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ትሰፋ ዘንድ ከልብ የሚፈልጉ ግልጥ የሆኑ ድርጅቶች መሆናቸውን አሳስባቸው፡፡

ከዚህ በታች የምናገኘው በተሳታፊዎች ማኑዋል የምናገኘውን የአንድ ድርጅት ግብአት ዝርዝሮችን እና የአንድ ስርአት ቁልፍ ጽንሰ-አሳቦችን ነው፡፡ እነዚህን ግብአቶች እና ጽንሰ-አሳቦች በተሳታፊዎች ማኑዋል በገጽ 25-27 ከሚገኙት ሶስት ስዕላዊ መግለጫዎች ጋር በማያያዝ አብራራ፡፡ የራስህ የሆኑ ምሳሌዎችን በመጠቀም ግብአቶችን እና ጽንሰ-አሳቦችን አስረዳ፡፡

ስዕላዊ መግለጫ 2፤ የአንድ ማህበረምዕመን ውስጣዊ ግብአቶች

ክርስቶስ ራስ የሆነበት ቤተክርስቲያን

ክፍለድርጅት፤ ድርጅት




የሰዎች ፍሰት፤ እንኳን ደህና መጣችሁ - ተሳትፎ - አገልግሎት

ውስጣዊ ይዘት፤ ቤተክርስቲያን ድርጅት እንደመሆኗ መጠን ተግባሯን የሚያውኩ የተለያዩ ክፍሎች አሉ፡፡ መሪዎች፣ መርሃ ግብሮች/ፕሮግራሞች፣ አባላት እና ግብአቶች አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አላቸው፡፡

ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ መሪነት በታች የምትገዛ ስትሆን ዓላማዋም ወንጌልን መመስከር እና መኖር ሲሆን በዚህም ሰዎች ክርስቶስን እንደጌታና አዳኝ እንዲቀበሉት ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ መሪነት፣ የምዕምናን አደረጃጀት፣ አባላት፣ መርሃ ግብሮች/ፕሮግራሞች፣ የመግባቢያ መንገዶች እና የግብአት አጠቃቀምን የመሳሰሉ ንኡስ አደረጃጀቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ንዑሳን አደረጃጀቶች የቤተክርስቲያንን ተልዕኮ ለማሳካት ሲንቀሳቀሱ እና በትክክል ሲተገበሩ የግለሰቦች እና የማህበረሰብ ሕይወት በወንጌል ኃይል ይለወጣል፡፡ በአንድ ንዑስ አደረጃጀት ውስጥ የሚፈጠር ችግር ሌሎችንም ሊያናጋ ይችላል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ደግሞ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ያላቸው የእርስ በእርስ ትስስር እና መደጋገፍ ነው፡

- በእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ውስጥ የቤተክርስቲያኒቱን ተግባራት ላይ በጎም ይሁን በጎ ያልሆነ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ንኡስ ስርአቶች አሉ፡፡

**ተግባር፡-**

የቤተክርስቲያናችሁን ንኡስ ስርአቶችን አስተዋውቁ (መርሃ-ግብሮች/ፕሮግራም፣ አገልግሎት ዘርፎች፣ ኮሚቴዎች፣ ወ.ዘ.ተ…)፡፡ እንዴት ነው አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የሚዛመዱት?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

ከቤተክርስቲያን መሪዎችህ ጋር በመሆን ክትትል አድርግ፡-

- የቤተክርስቲያንህን የተለያዩ የአደረጃጀት ክፍሎች እና የእያንዳንዱ ክፍል በረከቶች እና ተግዳሮቶችን ለይ፡፡

ጥምረት እና የእርስ በእርስ ጥገኝነት፤ የአብድ ስረአት ንኡስ ክፍሎች አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የሚዛመዱና አንዳቸው በሌላቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው፡፡ በአንድ አጥቢያ ውስጥም እንዲሁ በአንድ የአገልግሎት ዘርፍ የሚፈጠር ማንኛውም ጉዳይ ሌሎች የአገልግሎት ክፍሎች ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡ ለምሳሌ የቤተክርስቲያን የገንዘብ አቅም ሲዳከም የሌሎች መርሃ ግበሮች/ፕሮግራሞች እና የአገልግሎት ዘርፎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በመፍጠር ሰዎች ያላቸውን የጸጋ ስጦታ በመጠቀም የቤተክርስቲያኒቱ በረከት እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

ዓላማ፤ እያንዳንዱ ስርአት የተገኘበት አንድ የተለየ ዓላማ አለው፡፡ የቤተክርስቲያን ዓላማ እግዚአብሔር በቃሉ አማካይነት ባስተማረን ትምህርት የተወሰነ ነው፤ ይህም በክርስቶስ ስለሚገኝ ሕይወት መልካም ዜና ማወጅና ሰዎች እንደእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲኖሩ ማስተማር ነው፡፡ (ማቴ 28፡19-20) ቤተክርስቲያን ደቀመዝሙር የማድረግን ተልዕኮዋን ቸል ስትል እግዚአብሔር በነደፈው/ባቀደው የሕይወት መንገድ መኖር ያቅታታል፡፡

መረጋጋት እና ሚዛናዊነት፤ ሁሉም ስርአት ለውጥን የመቃወም ዝንባሌ አለው፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥም ሰዎች "በፍጹም በዚህ መንገድ ነገሮችን ከውነን አናውቅም" በማለት ለውጥን ሲቃወሙ እንመለከታለን፡፡ ሰዎች አዳዲስ የመተግበሪያ መንገዶችን ከማማር የለመዱትን የድሮውን መንገድ ማስቀጠል ይመርጣሉ፡፡ መሪዎች የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ለውጥን እንዲረዱና የለውጡ ደረጃ አግባብነት ያለው እንደሆነ ይመለከቱ ዘንድ ማስቻላቸውን ልብ ሊሉ ይገባል፡፡

አቻ-ፍጻሜ፤ እንደርስበታለን ብለን ያስቀመጥነውን አንድ ግብ ብዙ መድረሻ መንገዶች ኖሩታል፡፡ ይህም ስርአቶች ሊለወጡ የምትችሉ እና ማሻሻያ ሊደረግባቸው የሚገባ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ ለምሳሌቤተክርስቲያን ለመበለቶች/ባሎቻቸውን ላጡ እናቶች የሚሆን ቀለብ መሸመት አትችል ይሆናል፤ ነገር ግን እነዚህ እናቶች ተንቀሳቅሰው ይሰሩ ዘንድ፤ ልጆቻቸው ትምህርታቸውን እንዲያጠኑ የሚያግዟቸው ወጣቶችን ወይንም ፈቃደኛ የሆኑ የቤተክርስቲያን አባላትን ማስተባበር ትችላለች፡፡

መጠባበቂያ እቅድ፤ ማንኛውም ድርጅት ስለሚሰራበት አካባቢ እርግጠኛ መሆን ስለማይችል ሁሌም ለሚያወጣው እቅድ የሚሆን መጠባበቂያ እቅድ የማውጣት አቅም ያስፈልገዋል- መጠባበቂያ እቅድ የምንለው ዋና ይሆናል ብለን ያሰብነው እቅድ በተለያየ ምክንያት በማሳካበት ወቅት ተከተን የምንጠቀምበት እቅድ ነው፡፡ ጤናማ የሆነ ስርአት ቀድሞ የተቀመጠው እቅድ ባልተሳካ ጊዜ ሁሉ ግቡን ለመምታት የሚያስችለው ተለዋጭ እቅድ ይኖረዋል፤ ለምሳሌ፡- አንድ ቤተክርስቲያን የጎዳና ላይ የወንጌል ስርጭት ለማድረግ እቅድ ብትይዝና ይህን ለማድረግ ድንገት ዝናብ ወይንም ሌላ ገጠመኝ ይህን እቅድ ቢያስተጓጉል ያሰቡትን የሚያደርጉበት ሁለተኛ እቅድ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ህዳሴ/ለውጥ፤ እያንዳዱ ንዑስ ድርጅት አንድ የተለየ ዓላማን ለማስተግበር ያገለግላል፡፡ የቤተክርስቲያን ዓላማ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታቸውን አና ማህበረሰባቸውን ይለውጥ ዘንድ ሰዎችን ወደ እርሱ ማምጣት ነው፡፡

ይህ ስዕላዊ መግለጫ በአንድ ምስል ውስጥ ውስጣዊውንም ሆነ ውጫዊውን ይዘት ያሳያል፡፡

- ወደ ቤተክርስቲያናቹ 5፣ 10 ወይንም 15 ቤተሰብ በአንድ ጊዜ ቢመጣ በዚያች አጥቢያ ምን የሚከሰት ይመስለችኋል?
- ወደ ቤተክርስቲያን ከሚመጡ ሰዎች መካከል የመዘመር ወይንም የዝማሬ አምልኮን መምራት ስጦታ ያላቸው ይኖራሉ?
- ወደ እኛ የሚቀላቀሉ ሰዎች ጥሩ እና ተስማሚ ይሆናሉ?
- ጠንካራ አሳብ የሚሰነዝሩ ጥቂት ሰዎች ይኖሩ ይሆን?
- አሳሳቢ ችግር ያለባቸው ሰዎችስ ይኖሩ ይሆን?
- ሃሜተኛ የሆኑስ ይመጣሉ?

እነዚህ ጥያቄዎች የቁጥር እድገት አሁን ያሉበትን ቤተክርስቲያን ላይ ተጽዕኖውን እንደሚያሳርፍ እንዲያስቡ ሊያደርጓቸው ይገባል፡፡ 80 አባላት ያሉት ቤተክርስቲያን በአመት 20 ወይንም 30 አዳዲስ አባላት ቢጨመሩ ቤተክርስቲያኒቱ ከፍ ያለ ለውጥ ከማስተናገዷም በላይ በአደረጃጀትም ላይ ለውጥ ያመጣል፡፡ መሪዎችም ይህ ለውጥ ቤተክርስቲያኒቱ ጤናማ በሆነ መንገድ ታድግ ዘንድ የሚረዳ ይሆን ዘንድ ለውጡን በሚገባ ለማስተናገድ የሚያደርጉት ዝግጅት መተኪያ የሌለው ነው፡፡ ይህ እድገት በትክክል ካልተመራ ሰዎች ቤተክርስቲያንን ትተው ስለሚወጡ ቤተክርስቲያን እንዳታድግ ይሆናል፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡት ሁለት ምሳሌዎች የቤተክርስቲያንን እድገት ሚዛናዊ የማድረግን አስፈላጊነት አጉልተው ያሳዩናል፤


- በሾርባ ውስጥ ዝም ብለን ጨው ብንሞጅርበት ጣዕሙን ያጣል፡፡ ብዙ ጨው ለመጨመር ሾርባውን ለመስራት የሚሆኑትን ውሃ፣ አትክልቶች፣ ስጋ እና ሌሎች ቅመማቅመሞችን መጨመር በፈለግነው ጨው ብዛት ልክ በርከት አድርገን መጨመር ጣዕሙን የጠበቀ ሾርባ ለመስራት ያስፈልገናል እነጂ ዝም ብለን ጨው መጨመር አያስፈልገንም፡፡የሰው አካል ስርዓት ጤናማ እንዲሆን ሁሉንም ነገር ዛናዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ልባችሁ በጣም ጤናማ ቢሆን ነገርግን ጉበታችሁ ጤናማ ባይሆን ጠንካራ ልብ እንዲኖራችሁ አያደርግም፡፡ ደህነኛ ለመሆን ከፈለግን ሁሉም የሰውነት ክፍላችን ጤናማ መሆን ይኖርበታል፡፡

ስእላዊ መግለጫ 3፤ ውጫዊ እና ውስጣዊ ግብአቶች - ለውጥ

**ክርስቶስ ራስ ሆኖ የሚመራት ቤተክርስቲያን**

ክፍለ-ድርጅት፤ ድርጅት

የእግዚአብሔር መንግስት የእግዚአብሔር መንግስት




አስተያየቶች እና ውጤቶች

- አዎንታዊ ለውጥ በአንድ አጥቢያ እና ማህበረሰብ የሚመጣው በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ያሉ ንኡሳን ክፍሎች የቤተክርስቲያኒቱን ተልዕኮ ላሉበት አውድ ተገቢ በሆነ መንገድ ሲተገብሩት ነው፡ ፡
- የአንድ ቤተክርስቲያን ተጠባቂ አዎንታዊ ለውጥ ሊያዘግም ወይንም ከነጭራሹ ሊቆም የሚችለው እያንዳንዱ ንኡስ ክፍል ቀድሞ የተቀመጠውን ራዕይ እና ተልዕኮ በትኩረት መመልከት እና ወደዚያም መገስገስ ሲያቅተው ነው፡፡

የአንድ ስርአት ቁልፍ ግብአቶች

- አውድ
- ጥምረት እና አንዱ በሌላው ላይ ጥገኛ መሆን
- ዓላማ
- መረጋጋት እና ሚዛናዊነት
- አቻ-ፍጻሜ
- መጠባበቂያ እቅድ

ጤናማ ቤተክርስቲያን አዳዲስ ሰዎችን የምትቀበልበት፣ የምታሳትፍበት፣ በእምነታቸው እንዲያድጉ የምትንከባከብበት እና የጸጋ ስጦታቸውን ይጠቀሙ ዘንድ የምታስችልበት መንገዶች አሏት፡፡

ጤናማና የምታድግ ቤተክርስቲያን በቋሚነት በተወሰነ የጊዜ ርቀት በስሯ የሚገኙ የተለያዩ ስርአቶች ጤናማ ስራ እየከወኑ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ሁሌም ስላሉበት አውድ ይማራል፣ መርሃ ተግባሮች/ፕሮግራሞች እንዴት እየተተገበሩ እንዳሉ ይመዝናል፣ የቤተክርስቲያኒቱ ሃብት እና ንብረት በትክክል ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሆነ ይቆጣጠራል ወ.ዘ.ተ…

**ከቤተክርስቲያንህ መሪዎች ጋር በመሆን ክትትል አድርግ፡-**

የትኞቹ የቤተክርስቲያናችሁ የአገልግሎት ክፍሎች በሚገባ ይሰራሉ፤ የትኞቹስ የማሻሻል ስራ ይፈልጋሉ፡፡

- የቤተክርስቲያናችሁ መሪዎች በሙሉ በአካባቢው ስለሚኖሩ ማህበረሰቦች የሚያውቁትን ሁሉ በዝርዝር እንዲጽፉ አድርግ (ዝንባሌአቸውን፣ ፍላጎታቸውን ወ.ዘ.ተ… )
- በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎች ስለቤተክርስቲያን ያላቸውን አመለካከት በበለጠ ለማወቅ ቃለመጠይቅ አድርግ፡፡
- ስለአለህበት አውድ በበቂ ሁኔታ ታውቃለህ?
- መሪዎች ከማህበረምዕመኑ ጋር ጥሩ የሚባል ተግባቦት አላቸው?
- ማህበረምዕመናችሁ የጸጋ ስጦታቸውን ይጠቀማሉ?
- መሪዎች በቤተክርስቲያኒቱ ራዕይ እና ተልዕኮ ላይ አትኩረው ይሰራሉ ወይስ ሌላ ትኩረታቸውን የወሰደ ጉዳይ አለ?

*መልመጃ፤ "ቀዩ ምንጣፍ"*

ከሃያ ዓመት በፊት "ሊቪንግ ዋተር" የለች ቤተክርስቲያን ያሰራችውን አዲስ ሕንጻ አስመረቀች፡፡ ታዲያ ከዲያቆናት መካከል አንዱ የሆነው ሚሼል ስሚዝ የተባለ የ67 ዓመት አዛውንት ለማምለኪያ አዳራሹ የሚሆን ቀይ ምንጣፍ እንዲገዛ ሙሉ ወጪውን ቻለ፤ ታዲያ ምንጣፉ ቀይ እንዲሆን የመረጠው ራሱ ሚሼል ነበር፤ ምክንያቱም ቀይ የእርሱ ተወዳጅ ቀለም ስለሆነ፡፡ ሰው ሁሉ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ተጽዕኖአቸው ከፍ ያለ ስለነበር፤ የእነርሱን እና የቤተሰቡን ምርጫ በአክብሮት ተቀበሎ ቀዩ ምንጣፍ በማምለኪያ አዳራሹ ውስጥ ተነጠፈ፡፡

*መልመጃ፤ ቀዩ ምንጣፍ*

*ይህ መልመጃ የክፍለትምህርት 4 በጣም ወሳኝ ምዕራፍ ነው፡፡ የተዘረዘሩት ጥያቄዎች ብዙ ውይይት እና ትምህርት ሊያመነጭ ይገባል፡፡ በተሳታፊዎች ማኑዋል ላይ የሰፈረውን መረጃ አንብብ፣ መልመጃውን አብራራ ከዚያም ተሳታፊዎችን ከ5-8 ሰዎች ባሉት ትንንሽ ቡድን ክፈላቸውና ከዚህ በታች የቀረበውን ጥያቄ እንዲመልሱ አድርግ፡፡ ይህን ልምምድ ለማጠናቀቅ ከ20-30 ደቂቃ ያስፈልጋል፡፡*

*የዚህ ልምምድ ዋና ዓላማ ተሳታፊዎች ቤተክርስቲያን አገልግሎት ዘርፎች ላይ የሚወሰን ውሳኔ የቤተክርስቲያኒቱን ሌሎች ብዙ ጉዳዮች እንደሚያናጋ እንዲረዱ ነው፡፡ ዋናው ጉዳይ ለተፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ መፈለግ ሳይሆን ተሳታፊዎች በማህበረምዕመናቸው ውስጥ የሚፈጠር ማንኛውም ጉዳይ ውስብስብነት እንዲሁም እያንዳንዱ ውስኔ የቤተክርስቲያኒቱ የተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋል፡፡*

*በልምምዱ ማብቂያ (ጊዜ የሚፈቅድ ከሆነ) ለሶስት ወይንም አራት ቡድን አንዳንድ ተወካይ በመምረጥ ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ለእያንዳንዱ የተሰጡትን መልስ ለጠቅላላው ተሳታፊ በማቅረብ ለመለሱት ጥያቄ የሚሆን መፍትሄ ብለው ያነሱትን አሳብ እንዲናገሩ እድል ስጥ፡፡*

ከሃያ አመት በኋላ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ የተቋቋመው የሕንጻ ኮሚቴ ቀዩን ምንጣፍ በማንሳት የወለሉን ንጣፍ በሳምንቱ የስራ ቀናት አዳራሹን ለሌሎች አገልግሎቶች (ለምሳሌ፡- የልጆች ክለብ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ችግረኞች ለመመገብ) ለመጠቀም በሚያስችል ሌላ ንጣፍ ለመቀየር ተስማሙ፡፡ እናም እነዚህ የሕንጻ ኮሚቴ አባላት ያሰባሰቡትን የማምለኪያ አዳራሹን ንጣፍ የመቀየር ገንዘብ እንዴት አድርገው መጠቀም እንዳለባቸው ያስባሉ፡፡ በዚህ ወቅት ከሃያ አመት በፊት የ67 ዓመት ሰው ሆኖ ወጪውን ሸፍኖ ምንጣፉን የገዛው የአሁኑ የ87 አመት አረጋዊ ከፍተኛውን መዋጮ ለዚህ አገልግሎት ክፍል በማዋጣት፤

አሁንም ቀይ ምንጣፍ እንዲገዙ እና እንዲያነጥፉ ጠየቀ፡፡ የእርሱ ቤተሰቦች ይህን ጥያቄውን ሙሉ ለሙሉ ደገፉት፤ የሕንጻ ኮሚቴው ደግሞ ለሁለገብ አገልግሎት የሚሆን ወለል ንጣፍ እንዲሆን ምርጫቸው ሆነ፡፡

በዚህ መሃል መጋቢው ስጋት አድሮበታል፤ በአንድ በኩል ሚሼል እና ቤተሰቡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ተጽዕኖ በሚገባ ይገነዘባል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለሕንጻ ኮሚቴው የማምለኪያ አዳራሹ ንጣፍ ለሁለገብ ግልጋሎት እንዲሆን እንዲያስተካክሉት ሙሉ ኃላፊነት ሰጥቶ እንዲሰሩ ያደራጃቸው ራሱ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ማመን የከበደው፤ በማህበረሰቡ ውስጥ ብዙ ችግሮች እያሉ ሰዎች ሽንጣቸውን ገትረው ስለወለል ንጣፍ ክርክር መግጠማቸውን፤ ከዚህም ሲከፋ ከሁለቱም ወገን እነርሱ በሚሉት መንገድ ውሳኔ ካልተወሰነ ቤተክርስቲያን እንለቃለን እያሉ የሚዝቱ ሰዎች መኖራቸው ነው፡፡

ሀ. የሚሼል ዘመድ የሆነና ለረጅም ጊዜ ቤተክርስቲያን መጥቶ የማያውቅ አንድ ሰው የሚሼልን ስጦታ የሕንጻ ኮሚቴው የማያከብር ከሆነ ከዚህ በኋላ ደግሞ ወደዚህች ቤተክርስቲያን ዝር እንደማይል ማስጠንቀቂያ አዘል መልዕክቱን አስተላለፈ፡፡

ለ. ለረጅም ጊዜ በሴቶች ህብረት ውስጥ በማህበረሰቡ ያሉ ሰዎችን በወንጌል በመድረስ ታገለግል የነበረች እህት፤ ኮሚቴው የአንድን ሰው ምኞት ቤተክርስቲያን ሌሎችን ለማገልገል ካላት ፍላጎት የሚያስቀድም ከሆነ፤ እርሷም በበኩሏ የሚሆናትን ቤተክርስቲያን መፈለግ እንዳለባት ማሳወቅ ጀመረች፡፡

መ. ልጆቻቸው በቤተክርስቲያን ትምህርት እንዲያድጉ የሚፈልጉ ብዙ ቤተሰቦች፤ ቤተክርስቲያን ለልጆች አገልግሎት ትኩረት መስጠት እንዳለበት ያሳስቡ ጀመር፡፡

ይህች ቤተክርስቲያን የገጠማትን ችግር ይበልጥ ያወሳሰበው ደግሞ የሚሼል መታመም እና የልብ ቀዶ ህክምና ማድረጉ ነው፡፡

የሕንጻ ኮሚቴው ዛሬ ማታ በሚኖራቸው ስብሰባ መጋቢውን በጉዳዩ ላይ ለመያየት ጋብዘውታል፡፡

ከ3-5 የሚሆኑ ሰዎችን ያቀፈ ቡድን መስርቱ እና እናንተ በዚህ የሕንጻ ኮሚቴ ውስጥ እንዳላችሁና መጋቢውን በዚህ ጉዳይ ለማወያየት እንደምታገኙት አስቡ፡፡ ይህን ጉዳይ በጥልቀት ለማሰብ እና መፍትሄ ይሆናል የምትሉትን ሐሳብ ለማቅረብ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ተጠቀሙ፡-

1. በቤተክርስቲያኒቱ የተፈጠረው ይህ ሁኔታ በማህበረሰቡ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል? እንዴት?

2. የተፈጠረው ችግር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የቤተክርስቲያን አገልግሎቶችን ያናጋል? እንዴት?

ስፍራ/መገኛ　　መሪነት　　የድርጅቱ ታሪክ

ራዕይ/ዓላማ　　አባላት　　የቤተክርስቲያኒቱ እሴት

ሃብትና ንብረት　　መዋቅር　　ሌሎች ዘርፎች

መርሃግብር　　　　ከባቢ/ተግባቦት

3. ቤተክርስቲያኒቱ ምን አይነት ምርጫ አላት? የእያንዳንዱ ምርጫ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል?

4. እያንዳንዱን ስርአትን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ እንዴት ነው ይህን ውሳኔ ከራዕይዋ እና ከተልዕኮዋ አንጻር መወሰን የምትችለው?

ሰርቶ ማሳያውን ማጠቃለል

ለውጥን የምታመጣ ቤተክርስቲያን፡-

1. ለታላቁ ተልዕኮ ተገዢ ናት (ማቴ 22፡37)

- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ ውደድ
- ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ

2. ታላቁን ተልዕኮ ከግብ ታደርሳለች (ማቴ 28፡18-20)

- ሂዱና ሰዎችን ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው

*መደምደሚያ፤ በሰርቶማሳያው ማብቂያ*

*1. ተሳታፊዎች የመገምገሚያ ቅጹን እንዲሞሉ አድርግ*

*2. የሚቻል ከሆነ የሰርቶ ማሳያውን ሂደት የሚያሳዩ ፎቶዎችን ለብዜት መረብ አገልግሎት ላክ*

*3. ተሳታፊዎች በብዜት መረብ አገልግሎት የቀረቡትን ጤናማ ቤተክርስቲያን ልማት ሂደት እንቅስቃሴን እንዲገፉበት አበረታታቸው፡-*

- *ቤተክርስቲያንህን አጠናክር ከሚለው ሰርቶ ማሳያ በኋላ ማህበረምዕመኑ በግል የቤተክርስቲያኒቱን ጤናማነት የሚለካበት "የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት መዝን" የሚለውን ቅጽ ሙሉ፡፡ ይህን ለማግኘት የብዜት መረብ ድረገጽ ወይንም በአካባቢያችሁ ያለን የብዜት መረብ ተወካይ አነጋግር፡፡*
- *በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማሩ ወይንም ፍላጎት ያላቸው አብያተክርስቲያናት "ብዛት ያለው አጥቢያ" በሚለው መርሃግብር ያስፈልጋቸው ይሆናል፡፡*
- *መርሃግብሩን በጸሎት አጠቃልል፡፡*

*የአጥቢያ ቤተክርስቲያንን የተመለከተ መልዕክትን ለሚያስተላልፍ ሰው የቀረበው ዝርዝር መረጃ፤ ይህን ኮንፍረንስ ለአጥቢያ ቤተክርስቲያኑ ወይንም ለቤተዕምነቱ መስጠት የሚፈልግ መጋቢ በተሳታፊዎች መጽሐፍ በዚህኛው ገጽ እንዴት አድርጎ መምራት እንደሚችል መሰረታዊ የሆነው ቅደም ተከተል ተቀምጦለታል፡፡ እንዴት አድርጎ ለብዜት መረብ አገልግሎት የሚሆን ሪፖርት ማዘጋጀት እንደሚቻል ዝርዝ መረጃን ማግኘት ይቻላል፡፡*

*ወደፊት ይህን ሰርቶ ማሳያ የመምራት አቅም ያላቸው ሰዎችን በሚገባ በመመልከት እና ከልብ ማኖር አትርሳ፡፡ መሪዎች ምርጥ የሚባሉ እና እንዲህ ያለውን ስልጠና በየትኛውም ስፍራ በትክክል ሊያሰለጥኑ የሚችሉ፤ ከእነርሱ ጋር እንደቡድን መስራት የሚችሉ ሰዎችን በብዛት ለቀጣይ ሰርቶ ማሳያዎች ማዘጋጀትን ልብ ሊሉ ይገባል፡፡*

- አጥምቋቸው
- ኢየሱስ ያስተማረንን ትምህርት በሙሉ ያስተማረውን እንዲጠብቁ ማስተማር

እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን ለመውደድ፣ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉ ለመውደድ እና አግዚአብሔርን ማወቅ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ለመውደድ ተጠርቷል፡፡ ለውጥ የምታመጣ ቤተክርስቲያን ሁለንተናዊ ተልዕኮዋንና ዓላማዋን በሚገባ የተረዳች እና ክርስቶስን ለመከተል የመረጡ ሰዎችን ተከታትላ የምታሳድግ ናት፡፡

በዓለም ላይ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገች ያለች ቤተክርስቲያን ይህን ንግግር ፈጥሯል፡-

"ለታላቁ ትዕዛዝ እና ለታላቁ ተልዕኮ የሚሆን ታላቅ መሰጠት ታላቅ ቤተክርስቲያን ይመሰርታል፡፡"

ምዘና፤ እያንዳንዱ ሰርቶ ማሳያ የሚጠናቀቀው ተሳታፊዎች የምዘና/ግምገማ ቅጹን በመሙላት ይሆናል፡፡ የተሳታፊዎችን ምላሽ ውጤትን (የውጤቶቹን ጠቅለል ያለ አሳብ) እና አስተያየታቸውን በቅርብ ላለ የብዜት መረብ ተወካይ ወይንም በድረገጻችን www.multiplicationnetwork.org ይላኩልን፡፡

የምስክር ወረቀት፤ ብዙ ሰርቶ ማሳያዎች የሚጠናቀቁት ለተሳታፊዎች የምስክር ወረቀት በመስጠት ነው፡፡ እናንተም እንዲህ ማድረግ ከፈለጋችሁ በዚህ ማኑዋል የቀረበውን የምስክር ወረቀት ወይንም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ እና ይህን ሰርቶ ማሳያ በኃላፊነት ያስፈጸሙችን ቤተክርስቲያን አርማ የያዘ በማዘጋጀት መስጠት ትችላላችሁ፡፡

አባሪ፤ ስነመለኮታዊ መሰረቶች

ስቱዋርት ሙሬይ ስነመለኮታዊ መሰረትን በተመለከተ *Laying Foundations* በሚለው መጽሐፉ እንዲህ ጠቅለል አድርጎ አቅርቦታል፡፡ የሚያድግ ቤተክርስቲያንም ሆነ አዳዲስ የሚተከሉ የቤተክርስቲያናት ሁለቱም ቢያንስ በሶስት መሰረታዊ መርሆች ላይ መሰረታቸውን ያደርጋሉ፡-

1. በስጋ መገለጡ (ትስጉት/The Incarnation)

ልክ እግዚአብሔር በኢየሱስ በስጋ መገለጥ Incarnation ከሰው ጋር ራሱን አንድ እንዳደረገ፤ ቤተክርስቲያንም እንዲሁ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በአካል በመገኘት ፍላጎታቸውን በመሙላት የወንጌልን ሙሉ መልዕክት ማድረስ ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ቤተክርስቲያን በአንድ አካባቢ የሚገኝ የክርስቶስ አካል ናት፤ የማህበረሰቡ አካል በመሆን በክርስቶስ በሚገኝ ሕይወት የምስራች ወንጌል ትደርሳለች፡፡ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፤ ፊሊ 2፡5-8፤ ዮሐ 1፡1፣ 1፡14

"በታሪክ ውስጥ በርካታ ሰዎች እንደ አማልክት ለመሆን ሲፈልጉ፤ አንዱ እግዚአብሔር ግን ሰው ሆነ፡፡"

2. **MISSIO DEI (ሚሰዮ ዴይ): "GOD'S MISSION" "የእግዚአብሔር ተልዕኮ"**

የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ድህነት (መዳንን) እና ለውጥን ለማምጣት ያለማቋረጥ ድሆችን እና የጠፉትን የሚፈልግ አምላክ ነው፡፡ በተመሳሳይ ቤተክርስቲያንም ሰዎችን ደቀመዝሙር ማድረግ፣ ማህበረሰብን መለወጥ እና እግዚአብሔርን ወክላና ከእግዚአብሔር ጋር አሁን በዓለም ላይ እየሰራ ካለው ስራ ጋር ተባባሪ መሆኗ የእግዚአብሔር ተልዕኮ ስለሆነ ይህን ልትከተል ይገባታል፡፡

ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፤ ዮሐ 3፡16፤ ማቴ 28፡18-20፣ ማር 16፡15-16፣ ሉቃ 24፡46-49

"እሳት በመቀጣጠል ህልውናውን እንደሚያገኝ ሁሉ ቤተክርስቲያንም በተልዕኮ ትኖራለች"

3. የእግዚአብሔር መንግስት

ቤተክርስቲያን የምታውጀው እና ሰው ሁሉ እንዲመለከተው የምትጠቁመው፤ ኢየሱስ ያወጀውን እና ሰው ሁሉ ይመለከተው ዘንድ የጠቆመውን ነው - እርሱም፤ የእግዚአብሔር መንግስት መቅረብ! ቤተክርስቲያን የምትጠቁመው፣ ምልክት የምትሰጠው፣ በአካል የምትገልጠው እና የምታስተምረው እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ እና ልዕለተፈጥሮ እንደሆነ እና በፈጠራቸው ላይ ገዢ መሆኑን ነው፡፡

ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፤ 1ጴጥ 2፡9-12

ቆላ 1፡13

"...አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።"

- ኢየሱስ ክርስቶስ (ማቴ 6፡33)

**ማስታወሻ**

***መገምገሚያ ቅጽ፤***

1. ይህን ትምህርት እንዴት አድርጎ የቤተክርስቲያናችሁን ሰርቶ ማሳያ ፕሮግራም ሊደግፍ ይችላል?

☐ አጅግ በጣም ጥሩ ☐በጣም ጥሩ ☐ ጥሩ ☐ መካከለኛ ☐ደካማ

2. ይህን ሰርቶ ማሳያ ሌሎች እንዲማሩት ትመክራለህ?

☐ አዎን ☐ እንደሁኔታው ☐ አይመስለኝም ☐ አልመክርም

3. በዚህ ሰርቶ ማሳያ ላይ ምን ልታክልበት/ልትጨምርበት ትችላለህ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

4. ከዚህ ሰርቶ ማሳያ ምን ትቀንሳለህ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

5. የሰርቶ ማሳያውን መሪዎች በማስተማሩ ረገድ እንዴት ነበሩ?

☐ አጅግ በጣም ጥሩ ☐ በጣም ጥሩ ☐ ጥሩ ☐ መካከለኛ ☐ ደካማ

6. ስዕላዊ መግለጫዎቹ/ተንቀሳቃሽ ጽሑፎቹ ክፍለትምህርቱን ለመረዳት እግዘዋችኋል?

☐ በጣም አግዞኛል ☐ በመጠኑ አግዞኛል. ☐ አምብዛም ነው ☐ ምንም አላገዘኝም

7. የክፍለትምህርቱን ውጤት ያሳዩልኛል የምትሉትን ቁጥር አክብቡ፡-

| | ከፍተኛ ነጥብ | | | | ዝቅተኛ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|
| ክፍለትምህርት 1፤ መነሳሳት ራዕይ ተልዕኮ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ክፍለትምህርት 2፤ የጤናማ ቤተክርስቲያን አምስቱ መሰጠቶች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ክፍለትምህርት 3፤ የጤናማ ቤተክርስቲያን አምስቱ ተግባራት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ክፍለትምህርት 4፤ የለውጥ ስርአት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

8. ሌላ አስተያየት ወይንም ጥቆማ ካለ፡-

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**ወደፊት የሚተገበሩ ሰርቶ ማሳያዎች፤**

የቤተክርስቲያን መጋቢ ወይንም ክርስቲያን መሪ ከሆንክና ይህ ሰርቶ ማሳያ በምትመራው ቤተክርስቲያን እንዲደገም ከፈለግህ አሊያም ይህን ሰርቶ ማሳያ በማሰልጠን ለመሳተፍ ካለክ የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅብሃል፡-

1. ቤተክርስቲያንህን አጠናክር የሚለውን የአሰልጣኝ እና የተሳታፊዎችን ማኑዋል ከwww.multiplicationnetwork.org ላይ በነጻ በማውረድ ያንን መጠቀም፡፡

2. ይህን ስልጠና በቤተክርስቲያንህ ወይንም በምትመራው ቡድን ውስጥ ስትከውን ይረዳህ ዘንድ የብዜት መረብ አገልግሎቶች ተወካይን ጠይቅ፡፡

3. ሰርቶ ማሳያውን እንዳጠናቀክ፤ ያሰለጠንካቸውን ሰዎች ፎቶ እና የስልጠናውን ሪፖርት ብትልክልን መልካም ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የግምገማውን ጠቅለል ያለ ውጤት አንድትልክልን አንፈልጋለን፡፡ በቀላሉ ሪፖርት ልታደርግ የሚያስችልህ ቅጽ በድረ-ገጻችን ላይ ታገኛለህ፤ አስፈላጊ መስሎ ካልታየህ ደግሞ የሚከተሉትን መረጃዎች ከላክልን ይበቃል፡-

- የስልጠናውን ኩነት ሪፖርት ናሙና
- ሰርቶ ማሳያ፤ ቤተክርስቲያንህን አጠናክር
- ቀን
- የቤተክርስቲያኒቱ ስም
- የቤተክርስቲያኒቱ አድራሻ
- የመጋቢው ስም
- ስም (ስሞች) ስልጠናውን የመሩት ግለሰቦች/ግለሰብ
- የተሳታፊዎች ብዛት
- ጥቆማዎች ወይንም አጭር ምስክርነት
- የግምገማው ጠቅለል ያለ ውጤት

ሁልጊዜ አዳዲስ ሰዎች ይህን ስልጠና ቢያቀርቡ ብለን እንመኛለን፤ ቤተክርስቲያን ትበዛ ዘንድ!

እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ይጠቀምብኛል ብለህ ታስብ እንደሆን ከዚህ በታች ባለው ድረ-ገጽ እኛን በነጻነት ማግኘት ትችላልህ

multiplication network

*more churches, stronger churches*

*የዕውቅና የምስክር ወረቀት*

# ጠንካራ ቤተክርስቲያንን የመትከል መርህ

በተሰኘ ስርት ማሳያ ስልጠና አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ተሳትፈው ስላጠናቀቁ
ይህ የዕውቅና የምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል

ይህ ስልጠና በ____________________________ቤ/ክ/ ድርጅት ትብብር የተዘጋጀ ነው

የተሳታፊው ስም____________________________________________

ቦታ______________________________ ቀን__________________

*ለቤተክርስቲያን እድገት እና ለአዳዲስ ቤተክርስቲያናት ተከላ አገልግሎት የታለመ የመሪዎች ስልጠና*

WWW.multiplicationnetwork.org